ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

እሁድ 83ኛ ዓመት ቁጥር 020 መስከረም 20 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# “የእኛ ፍላጎት የተዋበች ኢትዮጵያን ሠርተን ለትውልድ ማሸጋገር ነው”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- እኛ የምንፈልገው ያማረችና የተዋበች ኢትዮጵያን ሠርተን ለትውልድ ማሸጋገር ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከትናንት በስቲያ ጅማ በመገኘት በልማት ላይ ያሉ ፕሮጀክቶችን ጎብኝተዋል ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የቀጣዩን “ገበታ ለትውልድ” ፕሮጀክት አስመልክተው ባደረጉት ንግግር፤ እኛ የምንፈልገው ያማረችና የተዋበች ኢትዮጵያን ሠርተን ለትውልድ ማሸጋገር ነው። ለዚህም ባለፉት ጊዜያት የሠራናቸው ሥራዎች ፍሬ እንዳፈሩ አይተናል። በዚህ ዓመትም በርካታ ፕሮጀክቶች ይመረቃሉ፤ አዲስ ፕሮጀክቶችም ይጀመራሉ ብለዋል።

“የእኛ ፍላጎት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## ኢትዮጵያ ከብሪክስ ተገቢውን ጥቅም ለማግኘት የሚጠበቁባት ዝግጅቶች

ገጽ 4

## በመዲናዋ በቀን 792 ሺህ ሜትር ኪዩብ ውሃ አምርቶ የማቅረብ አቅም ተፈጥሯል

ስምስም መንግሥቱ

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ከገፀምድርና ከከርሰምድር በቀን ወደ 792ሺ ሜትሪክ ኪዩብ ውሃ አምርቶ የማቅረብ አቅም መፍጠሩን ገለጸ፡፡ በዚህ ደረጃ አቅም ቢፈጠርም ከከተማዋ ነዋሪ የውሃ ፍላጎት ጋር ሲነጻጸር ገና ብዙ ሥራ እንደሚጠይቅም ተጠቁሟል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን የውሃ አቅርቦትና ሥርጭት ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ፍቃዱ ዘለቀ የውሃ አቅርቦትን ለማሻሻል እየተሠራ ያለውን ሥራ አስመልክተው ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደገለጹት፤ የውሃ አቅርቦትን ለማሻሻል በየአመቱ የሚሠሩት ሥራዎች ሽፋኑን ከፍ እንዲል ያስቻሉ ሲሆን፣

በመዲናዋ በቀን... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ፍቃዱ ዘለቀ፣

## ‹‹የመከላከያ ሠራዊት ግዳጅ አፈፃፀም አቅምን ለመገንባት ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን እየሠራን እንገኛለን››

-ሌተናል ጄኔራል ይመር መኮንን
የመከላከያ ትምህርትና ሥልጠና ዋና መምሪያ ኃላፊ

ገጽ 4





















## “በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ትግበራ ችግር እንዳያጋጥም ክትትል ይደረጋል”

- ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ
የኢትዮጵያ ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ሁለተኛው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ትግበራ ችግር እንዳያጋጥም ድጋፍና ክትትል ይደረጋል ሲሉ የኢትዮጵያ ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ ገለጹ፡፡

የኢትዮጵያ ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሁለተኛው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ወደተግባር ሲገባ የተለያዩ ችግሮች እንዳያጋጥሙ ኢንስቲትዩቱ በየጊዜው ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፡፡

እንደ ፕሮፌሰር በየነ ገለጻ፤ በሁለተኛው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ላይ በቀረቡ ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ምን ድክመት አለ?፣ ዕቅዱ ምን ውጤት ያስገኛል?፣ እንዴትስ መተግበር አለበት? በሚሉት ጉዳዮች ዙሪያ ጥናት ይደረጋል።

ኢንስቲትዩቱ በሚያከናውነው ጥናት መሠረት በቀጣይ ስለሚኖሩ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ጥልቀት ያለው መረጃ ለመንግሥት ይቀርባል ብለዋል።

የኢኮኖሚ ማሻሻያው የማክሮ ኢኮኖሚውን ለማረጋጋት፣ የግሉ ዘርፍ ንግድና የኢንቨስትመንት ከባቢን ለማሻሻል፣ የአየር ንብረትን ለውጥን በመቋቋም ምርታማነትን ለማሳደግና ብቃት ያለው የሲቪል ሰርቪስ መፍጠር ላይ ትኩረት እንደሚያደርግ ጠቁመዋል።

ኢንስቲትዩቱም በሀገር በቀል ማሻሻያ መሠረት የሆኑ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረጉ ምርምሮችን በማከናወን ለየችግሮቹ ጊዜውን የጠበቀ መፍትሄ እንዲቀመጥ ጥረት ያደርጋል ሲሉ ተናግረዋል።

ፕሮፌሰር በየነ እንዳመለከቱት፤ በጥናት የተለዩ የመፍትሄ ሃሳቦች ለመንግሥትና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት በየጊዜው እንዲደርስ ይደረጋል።

በቀጣይም ለሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ግብዓት የሚሆኑ በዕውቀት፣ በጥናትናና በመረጃ የተደገፉ ሃሳቦችን እንደሚያቀርቡ ገልጸዋል።

ኢንስቲትዩቱ በሀገሪቱ በሚቀረጹ ፖሊሲዎችን በጥናት የተደገፉ እንዲሆኑ ያግዛል፤ ፖሊሲዎች ተግባራዊ ከመደረጋቸው በፊት ጥናትና ምርምር የማድረግ ሥራ በዋናነት እያከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል።

በሀገሪቱ እየተተገበሩ የሚገኙ ፖሊሲዎች ድክመትና ጥንካሬ የመለየት ሥራ እንደሚከናወን ገልጸው፤ በቀጣይ ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸውን ፖሊሲዎችና የመፍትሄ ሃሳቦች ለሚመለከተው ባለድርሻ አካላት ይቀርባሉ ብለዋል።

የኑሮ ውድነት፣ የሥራ አጥነት፣ የአየር ንብረት ለውጥና ሌሎች ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ጥናትና ምርምር በማድረግ የመፍትሄ ሃሳብ የማስቀመጥ ተግባሩ በቀጣይም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል፡፡

በሌላ በኩል ኢንስቲትዩቱ ማህበራዊ ኃላፊነቱን ለመወጣት ባከናወነው ተግባር በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ አምስት እና 11 በአንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ብር ያሳደሳቸውን ቤቶች አስረክቧል።


# “በምርቶች ላይ የተደረጉ ያልተገቡ የዋጋ ጭማሪዎች በኑሯችን ላይ ጫና ፈጥሮብናል ”

## - የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች

## “በግብርና ምርቶች የተደረጉ የዋጋ ጭማሪዎች በቅርቡ ይስተካከላሉ”

## - ንግድ ቢሮ

**ሳሙኤል ወንደሰን**



አዲስ አበባ፡- በምርቶች ላይ የተደረጉ ያልተገቡ የዋጋ ጭማሪዎች ኑሯችንን ለመምራት ፈተና ሆኖብናል ሲሉ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ገለጹ። የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ በበኩሉ በግብርና ምርቶች የተደረጉ የዋጋ ጭማሪዎች በቅርቡ እንደሚስተካከሉ ገልፆ፤ ነዋሪዎች እሁድ ገበያዎች፣ የአትክልትና የፍራፍሬ ማቅረቢያ ማዕከላት በመሄድ ሊገበያዩ ይገባል ብሏል።

በኃይሌ ጋርመንት አትክልት ሲገዙ ያገኘናቸው ወይዘሮ ደስታ ሙሉጌታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ገበያ ነጋዴውንና ሸማቹ የሚያገናኝ ቦታ ነው። በዚህ ቦታ ሁሉም ተጠቃሚ ለመሆን የሚሞከርበት ቦታ ቢሆንም የደሃውን ማህበረሰብ አቅም የሚፈታተን ዋጋ ጭማሪ ማድረግ ተገቢ አይደለም። በተለይ ሀገር ውስጥ የሚመረቱ ምርቶች ላይ ከፍተኛ ጭማሪ በመደረጉ ምርቶችን ለመሸመት አቅማችንን የተፈታተነበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

“ኃይሌ ጋርመንት አትክልት ተራ ሽንኩርት ልገዛ ነበር። ነገር ግን ሽንኩርት ሳልገዛ ወደ ቤት እየተመለስኩ ነው” ያሉት ወይዘሮ ደስታ፤ አንድ ኪሎ ሽንኩርት በአንድ መቶ አስር ብር የመግዛት አቅሙም የለኝም ብለዋል።

በግል ትምህርት ቤት ውስጥ የጽዳትና የመልዕክት ሠራተኛ ሆኜ ኑሮዬን እየመራሁ ነው። ለጽዳትና ለመልዕክት ሠራተኛ ደመወዝ ሽንኩርት በኪሎ መቶ አሥር ብር መግዛት ከባድ ነው ያሉት ወይዘሮ ደስታ፤ የዋጋ ጭማሪን መንግሥት ብቻ ሳይሆን ሁሉም ሊያስብበት ይገባል ብለዋል።

አቶ አዳነው ካሳ በበኩላቸው፤ በክረምት የሽንኩርት አቅርቦት ዝቅተኛ ነው። ነገር ግን አንድ ኪሎ ሽንኩርት በሰማንያና በመቶ አስር ብር እየተሸጠ መሆኑ የኑሮ ውድነቱ እንዲባባስ አድርጎታል። በተመሳሳይ ቲማቲም እና የድንች ዋጋ የናረ በመሆኑ ነዋሪውን እያማረረ ነው ብለዋል።

የግብርና ምርቶች ዋጋ መጨመር እንጂ መቀነስ አይታይባቸውም። መንግሥት ገበያውን ለማረጋጋት በበዓላት ወቅት የሚሠራውን ሥራ አጠናክሮ መቀጠል አለበት እንጂ የበዓል ወቅት ተግባር ብቻ መሆን እንደሌለበት መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ተደጋጋሚና ገደብ የሌለው የዋጋ ጭማሪ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የማህበረሰብ ክፍሎች በእጅጉ የሚጎዳ በመሆኑ ሁሉም እርስ በእርስ ሊደጋገፍና ሊተባበር እንደሚገባ ተናግረዋል።

በኃይሌ ጋርመንት አትክልት ተራ ነጋዴ የሆነው አቶ ጀሚል ሀምዛ በበኩሉ፤ በተለይ የሽንኩት ዋጋ በእጅጉ መናሩን ጠቁሞ፤ በአሁኑ ጊዜ ከ85 እስከ 110 ብር ድረስ እየተሸጠ ነው ብለዋል።

ጉዳዩ ምንም ይሁን እንደዚህ አይነት ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ ሕዝብን የሚጎዳ ነው ያሉት አቶ ጀሚል፤ መንግሥት ይህንን የዋጋ ጭማሪ ለመከላከል የራሱ የሆነ ሥርዓት ቢፈጥር የተሻለ ይሆናል። ምርቶች በጥራትና በብዛት ቢመረቱ ገበያው ላይ የሚደረግ የዋጋ ጭማሪን መቆጣጠር እንደሚቻል ገልጸዋል።

ሌላው በክረምት ወቅት ሽንኩርት በብዛት አይመረትም። ይህም ለሽንኩርት የዋጋ ጭማሪ እንደአንድ መንስዔ ሊነሳ ይችላል ያሉት አቶ ጀሚል፤ አሁን ላይ ሸማቹ ሽንኩርት መግዛት ቀንሷል። ይህም በገበያው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እያሳደረ ነው። በዚህም ነጋዴው እየተቸገረ ነው ብለዋል።

ከዚህ ቀደም አንድ መኪና ሽንኩርት ወይም ድንች ለማምጣት ለትራንስፖርት የምንከፍለው ዋጋ ስድስት ሺህ ብር ነበር። አሁን ግን ከሃያ ሺህ ብር በላይ ደርሷል ያሉት ደግሞ የድንችና የሽንኩርት ነጋዴ የሆኑት አቶ ኤሊያስ ከድር ናቸው።

እንደ አቶ ኤሊያስ ገለፃ፤ የትራንስፖርት ዋጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው። በሚጨመረው ዋጋ ራሱ ምርት ከገበሬው ለማምጣት አሁን ባለው ወቅታዊ ሁኔታ ሹፌሮች ይፈራሉ። ይህም የሽንኩርት ዋጋ ላይ ከፍተኛ ጭማሪ እንዲኖር አድርጎታል። ከዚህም በተጨማሪ የሽንኩርት አቅርቦቱ በጣም ዝቅተኛ ነው ብለዋል።

ለዋጋ ጭማሪ መንስዔ የሚሆኑ ምክንያቶችን መንግሥት ከነጋዴና ገበሬ ጋራ በመተባበር መፍታት ይቻላል ያሉት አቶ ኤሊያስ፤ ህብረተሰቡ ላይ ተገቢ ያልሆነ የዋጋ ጭማሪ እንዳይደረግ የበኩሉን ሚና እንደሚያደርግ ተናግሯል።

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ሰውነት አየለ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ከተማ አስተዳደሩ ከአምራች አርሶ አደር ማህበራት እና ከክልሎች ጋር በመቀናጀት ለነዋሪው ሽንኩርት እያቀረበ ይገኛል። በዋነኛነት 72 የሚደርሱ የእሁድ ገበያ ቦታዎች አሉ።

ከዚህም በተጨማሪ በከተማ ውስጥ የተገነቡ ወደ አገልግሎት እየገቡ ያሉ የአትክልትና የፍራፍሬ ማቅረቢያ ማዕከላት ውስጥም የህብረተሰቡ የመግዛት አቅም ባማከለ ሁኔታ እንዲሸጡ እየተደረገ ነው። በዚህ ገበያ ላይ እንደየ ጥራት ደረጃው ሽንኩርት ከ47 ብር እስከ 62 ብር እየተሸጠ መሆኑን ገልፀዋል።

ከበዓሉ ወዲህ ጭማሪ መኖሩን እኛም ታዝበናል ያሉት ኃላፊው፤ በመደበኛ ገበያ ውስጥ አላስፈላጊ እና ምክንያታዊ ያልሆነ የዋጋ ጭማሪዎች መታየታቸውን ተከትሎ ከተማ አስተዳደሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ባዘጋጀባቸው ቦታዎች የእለት ተእለት ፍጆታቸውን እንዲገዙ አሳስበዋል።

በከተማዋ የተከሰተው የሽንኩርትና የሌሎች ምርቶች የዋጋ ጭማሪ በቅርቡ እንደሚፈታም ተናግረዋል።

# የኮንታ ህዝብ ከኮይሻ ፕሮጀክት ትልቅ ተስፋ ሰንቋል

**ግርማቸው ጋሻው**

በርካቶች አካባቢውን በማራኪ ውበቱ የተነሳ ምድረ ገነት ይሉታል። ይህ የውበት ማማ የሆነው የጨበራ ጩርጩራ ብሔራዊ ፓርክ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ከኮንታ እስከ ዳውሮ ዞን የተዘረጋ ነው። በተፈጥሮ ሀብቱ ውበትና ስብጥር የሰው ቀልብን ይገዛል፡፡

በዚሁ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል በኮንታ ዞንና አካባቢው በገበታ ለሀገር እየተከናወኑ ያሉ የቱሪዝም መስህብ ስፍራዎች ልማት ህዝቡ ትልቅ ተስፋ አጭሯል፡፡

መቶ አለቃ ኃይሌ ታደሰ በጨበራ ጩርጩራ ፓርክ በጥበቃ ሙያ እየሠራ ይገኛል። ቀደም ሲል የመከላከያ ሠራዊት አባል የነበረው መቶ አለቃ ኃይሌ፣ በአሁኑ ጊዜ በጨበራ ጩርጩራ ፓርክ ፀጥታና ደህንነት ሥራ ሲሠራ ነው ያገኘነው። በዚህ ሥራው 4000 ወርሀዊ ደመወዝ ይከፈለዋል። ይህ ግን ኑሮውን ለማሸነፍ በቂ አይደለም።ወደፊት ፓርኩ ሲለማ የቱሪስት ፍሰቱ ስለሚጨምር የእኔም ገቢ ያድጋል ብሎ ተስፋ ሰንቋል፡፡

ኤደኖ ቤተላ የጨበራ ጩርጩራ ፓርክ የእስካውቶች አስተባባሪ ነው። የደንና እንስሳት ጥበቃ ሠራተኛ ሆኖ ከተቀጠረ 16 ዓመታት ሆኖታል። በፓርኩ የሚገኙ በርካታ ዕፅዋትና እንስሳት ከሕገወጥ አደን የምንጠብቀው ፓርኩ ለእኛም ሆነ ለሀገር ኢኮኖሚ የሚኖረውን ትልቅ አስተዋጽኦ በመረዳት ነው ብሏል፡፡

የገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች ቀደም ሲል ትኩረት ሳይሰጣቸው ከቆዩ እንደ ጨበራ ጩርጩራ አይነት እምቅ የቱሪዝም ሀብት የሚገኝባቸው ስፍራዎች ጎልተው እንዲወጡና እንዲለሙ እድል ፈጥሯል። በዚህም በርካታ ወጣቶችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች የሥራ ዕድል ፈጥሯል የሚሉት የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ ሰላማዊት ካሳ ናቸው፡፡

በጨበራ ጩርጩራ ፓርክ በግልና በመንግሥት እየተገነቡ ያሉ የቱሪዝም መሠረተ ልማቶች ለዘርፉ እድገት ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፡፡

በዞኑ ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ የቱሪዝም ዘርፍን የሚያነቃቃ ተግባራት እየተካሄደ እንደሚገኝም የገለፁት ደግሞ የኮንታ ዞን አስተዳዳሪ አቶ ነጋ አበራ፤ ዞኑ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ቅርስ ባለቤት ቢሆንም ባለፉት ዓመታት ትኩረት ተነፍጎት በመቆየቱ ከዘርፉ ጥቅም ማግኘት አልተቻለም ብለዋል።

ከዚህ በፊት ምንም አይነት የቱሪስት ፍሰት ያልነበረ ሲሆን አሁን ላይ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በታቀደው ገበታ ለሀገር ፕሮጀክት አካባቢው በመካተቱ ህብረተሰቡ ትልቅ ተስፋ ሰንቋል ነው ያሉት፡፡

ቀደም ሲል አካባቢው በሚዲያ ባለሙያዎች የመጎብኘት እድል እንዳላገኘ የገለፁት ኃላፊው፤ ጉብኝቱ አካባቢው በዘርፉ ያለውን እምቅ አቅም በማሳየት የሀገር ውስጥ ጎብኚዎችን ለማነቃቃት ከፍተኛ ፋይዳ እንደሚኖረው ተናግረዋል።

ዞኑ የተለያዩ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶች ባለቤት መሆኑን ገልጸው፤ ከገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች አንዱ በሆነው ይህ ስፍራ ያሉንን የተፈጥሮ ሀብቶች ወደ ልማት መቀየር እንደሚቻል ማሳያ እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

እስካሁን በተደረገ ጥናት በፓርኩ ከ40 በላይ ትላልቅና መካከለኛ አጥቢ የዱር እንስሳት ከአውራሪስ በቀር የአፍሪካ ዝሆኖች፣ ጎሾች፣ ጉማሬዎች፣ አንበሳ እንዲሁም ብርቅዬ የአዕዋፍና የዓሣ ዝርያዎች፣ ፍል ውሃዎች፣ ፏፏቴዎች፣ ዋሻዎችና ሌሎችም የተፈጥሮ ሀብቶች እንደሚገኙ ጠቅሰዋል።

ከጅማ እስከ አመያ ያለው መንገድ አስቸጋሪነት፣ የመብራትና የቴሌኮም አገልግሎቶች መቆራረጥን እንደ ተግዳሮት ያነሱት የዞኑ ኃላፊ፤ መንግሥት እነዚህን መሠረተ ልማቶች በማሟላት ረገድ ትኩረት ሰጥቶ ሊሠራ እንደሚገባ አመልክተዋል፡፡

የጨበራ ጩርጩራ ብሄራዊ ፓርክ በኮንታና ዳውሮ ህዝቦች ፍላጎትና ጥያቄ በ 1997 ዓ.ም የተመሠረተ ሲሆን 1410 ኪ.ሜ የሚሸፍን የቆዳ ስፋት አለው።ፓርኩ ከአመያ ከተማ በ 13 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ስለሚገኝ ለቱሪስቶች ምቹ ነው።ፓርኩ ከአዲስ አበባ 454 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል፡፡

ኮንታ ዞን የሚገኘው የጨበራ ጩርጩራ ፓርክና በስፍራው የሚገኙ የተለያዩ የቱሪስት መስህቦችና የመሠረተ ልማት ግንባታ ሥራዎች ሰሞኑን በጋዜጠኞች ቡድን ተገብኝቷል።በሚዲያ ባለሙያዎች ከተጎበኙት የቱሪስት መዳረሻዎች መካከል የመንገድና የድልድይ እንዲሁም የቱሪስቶችን ቆይታ ሊያራዝሙ የሚችሉ የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ተጠቃሽ መሆናቸው ታውቋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ቱሪዝምን ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር የሀገርን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ ይገባል!

ኢትዮጵያ በርካታ ተፈጥሯዊ፣ ሰው ሠራሽና ባህላዊ ቅርሶችን በዩኔስኮ በማስመዝገብ በአፍሪካ ቀዳሚዋ ሀገር ናት። የተመዘገቡ እና ያልተመዘገቡ ሌሎች በርካታ ጥንታዊ ቅርሶችና የቱሪዝም መስህቦችም ባለቤት ናት።

ነገር ግን ግን ሀገሪቱ ኢትዮጵያ በተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች የበለፀገችና በርካታ የቱሪስት መስህብ ያላት ሀገር እንደመሆኗ ዘርፉ አድጓል ለማለት ጊዜው ገና ነው። ለዚህ አንዱ ማሳያ በዩኔስኮ በተመዘገቡ ቅርሶች ብዛት ከኢትዮጵያ የሚያንሱ ሆነው በጎብኚዎች ቁጥር ግን ከኢትዮጵያ የሚበልጡ የአፍሪካ ሀገራት መኖራቸው ነው።

ኢትዮጵያ ካላት እምቅ የቱሪዝም አቅምና መዳረሻዎች አንፃር እያገኘችው ያለው ጥቅም እጅግ አነስተኛ መሆኑ ግን ድብቅ አይደለም፡፡ ለዚህ ደግሞ አንዱና ትልቁ ችግር በቱሪስት መዳረሻ ስፍራዎች ያሉ የመሠረተ ልማትና ደረጃቸውን የጠበቁ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት እጥረቶች ናቸው፡፡

ዘርፉን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር በተፈጥሮ መሰጠትንም ጥረትንም ይጠይቃል። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ቱሪዝም ኢንዱስትሪ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እመርታ እያሳየ እንደሚገኝ መካድ አይቻልም። መንግሥት ለቱሪዝም ኢንዱስትሪ ዘርፍ ልዩ ትኩረት ሰጥቷል። በዚህም በተፈጥሮ የሚገኝ የሰዎችን ቀልብ የሚማርኩ፣ ለምርምር የሚገፋፉ ጸጋዎችን ወንዝ፣ ሃይቅ፣ መልከዓምድራዊ አቀማመጥ፣ የአየር ንብረት፣ ደን፣ እጽዋትና እንስሳት፣ ባህል፣ ወግና ቋንቋ፣ ታሪክና ታሪካዊ ቅርሶችን ለቱሪዝም ለመጠቀም አበረታች ጅምሮች እየታዩ ነው።

እነዚህ የተፈጥሮ ስጦታዎች ግን በራሳቸው ቱሪስቶችን ለመሳብና ለማሰንበት በቂ አይደሉም። ከማስተዋወቅ ጀምሮ የተለያዩ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትና መሠረተ ልማቶች ያስፈልጋሉ። የተለያዩ ሀገራት ዜጎች ለትምህርትና ለጤና አገልግሎት፣ ለምርምር እንዲመጡ ማድረግ የሚያስችሉ ጥራት ያለው አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት፣ ዓለም አቀፍ ጉባዔዎችን ማካሄድ የሚያስችሉ መሠረተ ልማቶች ያስፈልጋሉ፡፡

በብሔራዊ ፓርኮች ያለውን የመሠረተ ልማት ደረጃ ማሻሻል፣ ፓርኮችና ሎጆችን ከዋና መንገድ ጋር የሚያገናኙ መጋቢ መንገዶችን ደረጃ ማሻሻል፣ እንዲሁም በፓርክና በእንስሳት መጠበቂያ የሚገኙ የዱር እንስሳት አደንን መከላከል፣ ቅርሶች የሚገኙበትን አካባቢ መጠበቅና የመሳሰሉ ሥራዎች ትኩረት ይፈልጋሉ። ከዚህ በተጓዳኝ የቱሪዝም ሚኒስቴር የተፈጥሮና ባህላዊ ቅርሶችን በመንከባከብና በማልማት፣ የባህልና የቱሪዝም ቁሳቁሶችን ለገበያ በማቅረብ፣ የአገልግሎት አሰጣጥን የላቀ በማድረግ፣ የባህልና የቱሪዝም የመረጃ ሥርዓት በማሻሻል፣ እንዲሁም የልማት አጋሮችን በላቀ ደረጃ ማቀናጀት ላይ ይበልጥ ሊሠራ ግድ ይገባል።

ቅርሶችን በአግባቡ በመያዝ፣ ለትውልድ በማሳየትና፣ የገቢ ምንጭ ከማድረግ አንጻር ብዙ ሥራ ይቀራል። ለዚህ ደግሞ የቱሪዝም መዳረሻዎችን ማስፋትና ማስተዋወቅ ላይ ያለው ክፍተት አንዱ ምክንያት ነው።

የሀገሪቱን የቱሪዝም ዘርፍ ለማሳደግ የአፈጻጸም አቅምን ማጠናከር እንደሚገባ ግልፅ ነው። ፖሊሲና ስትራቴጂን መሠረት ባደረገ መልኩ ቱሪዝምን ለሁሉም ዜጎች ተደራሽ ለማድረግ መሥራት ይገባል። መንግሥት የቱሪዝም ኢንዱስትሪውን ለዜጎች የሥራ ዕድል ፈጠራና የውጭ ምንዛሪ ምንጭ እንዲሆን ለማስቻል ለዘርፉ ልዩ ትኩረት ሰጥቷል። በዚሁ መሠረት የቱሪዝም ዘርፉን ለማልማት የታዩ ጅምሮች ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል።

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የቱሪዝም እምቅ አቅም ቢኖራትም ከዘርፉ ስታገኝ የነበረው ጥቅም እዚህ ግባ የሚባል አልነበረም። አሁን ይህ ሁኔታ እየተቀየረ ነው። መንግሥት ነባራዊ ሁኔታውን ለመቀየርና ዘርፉ በኢኮኖሚው ውስጥ ተገቢውን ድርሻ እንዲይዝ አስቻይ የሪፎርም ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ለዘርፉ ዕድገት ምቹ መደላድል ለመፍጠር ፖሊሲዎችንና የሕግ ማዕቀፎችን ከማሻሻል ባለፈ ቱሪዝምን ከማኅበራዊ ዘርፍ ወደ ኢኮኖሚ ዘርፍ ማሸጋገር እየቻለ ይገኛል፡፡ በቀጣይነት ቱሪዝም ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ የሚያስችል ሰፊ የሥራ እድል መፍጠርና የውጭ ምንዛሪ ግኝትንም በጉልህ ሊያሳድግ የሚችል በመሆኑ የሀገር ውስጥና የውጭ ጎብኚዎችን ቁጥር ለማሳደግ የማስተዋወቅና ጉብኝትን የማነሳሳት ሥራ በከፍተኛ ደረጃ ሊሠራ ይገባል። የቱሪስቶችን የቆይታ ጊዜ ለማራዘም የመሠረተ ልማትና የቱሪዝም መዳረሻዎችን ለማስፋፋትም እየተሠሩ የሚገኙ እንደ ገበታ ለሀገር ፤ ገበታ ለሸገር ፤ ገበታ ለትውልድ አይነት ኢኒሼቲቮችና በርካታ ፕሮጀክቶች አይነተኛ ሚና እንደሚጫወቱ ይታመናል፡፡ ይህ ሲሆን የቱሪዝም ዘርፉ በተለይ አሁን በሀገሪቱ ጎልቶ የወጣውን የሥራ አጥነት ችግር በመፍታትና ሀገራዊ ገቢን በማሳደግ ህዝብን ቀጥተኛ ተጠቃሚ ማድረግ በማስቻል ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከት ይችላል!


**አዲስ ዘመን**

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## መስቀልን

## ከሺሕ ዘመን ታሪካችን እና ከኢትዮጵያ ቤ/ክ አንጻር በጨረፍታ. . .

በዲ/ን ተረፈ ወርቁ

የመስቀል የክርስትና ሃይማኖት ትልቅ ትእምርት/ሲምቦል ነው። መስቀል ከክርስትና ሃይማኖት ጋር ሺሕ ዘመናትን የዘለቀ፣ የጠበቀ ትስስር አለው። ወደ እኛው ታሪክ ስንመለስ ደግሞ ቅዱስ መስቀል በኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ትልቅ ክብር፤ ልዩ ስፍራ አለው።

ወደ ኋላ ተጉዘን ታሪክ መዛግብትን ስንፈትሽ፤ ክርስትና ሃይማኖት የሀገራችን ብሔራዊ ሃይማኖት በሆነበት በ4ኛው መቶ ክ/ዘመን የአክሱም/የኢትዮጵያ ነገሥታት የነበሩት ወንድማማቾቹ ኢዛና እና ሳይዛና በስመ ክርስትናቸው አብርሃ ወአጽብሃ በ፬ኛው መቶ ክ/ዘ የክርስትና ሃይማኖትን በይፋ ከተቀበሉና የመንግሥታቸው ሃይማኖት ባደረጉ ማግሥት በወርቅ ሳንቲሞቻቸው ላይ ቀድሞ ይጠቁሙበት የነበረውን የጨረቃ እና ሌሎች የግሪክ አማልክት ምስሎችን ወደ መስቀል መቀየራቸውን ያወሳሉ።

(በነገራችን ላይ የግሪክ ሥልጣኔ በዘመኑ እጅግ ገናና ከመሆኑ የተነሳ ሃይማኖታቸው/አማልክቶቻቸው፣ ቋንቋቸውና ባህላቸው መላውን ከዓለም ተቆጣጥሮት ነበር። ልክ እንደዛሬው እንግሊዝኛ የግሪክ ቋንቋም Linguafranka/ዓለም አቀፍ ቋንቋ ነበር። ኢትዮጵያውያን የግሪክ ቋንቋን ለዓለም አቀፍ ግንኙነት በሀገር ውስጥ ደግሞ ግእዝን እና የሳባውያንን ቋንቋዎችን ይጠቀሙ እንደነበርም ጥንታውያን የታሪክ መዛግብት በስፋት ይጠቁማሉ።)

በዘመኑ እጅግ ገናና የነበሩት ኢትዮጵያውያን/አክሱማውያን (በነገራችን ላይ በዘመኑ በዓለማችን ላይ ከነበሩ አራት የዓለማችን ታላላቅ ሥልጣኔዎች መካከል ከግሪክ፣ ከፐርሺያ/የአሁኗ ኢራንና ቻይና ሀገራት ጋር አክሱም/ኢትዮጵያ አንዷ የዓለማችን ታላቅ ሥልጣኔ እንደነበረች ልብ ይሏል፤) አክሱማውያን የአሁኗን የመንን ጭምር ሲገዙ የነበሩ ግዙፍ የባሕር ኃይል ባለቤቶች፣ ዓለም አቀፍ ንግድን ያሳልጡ የነበሩና በወርቅ ሳንቲም ይገበያዩ የነበሩ ታላቅና ሀብታም ሕዝቦች ነበሩ/ነበርን ልበል ይሆን... ከታሪካችን አንድ ሰበዝ እንምዘዝ እስቲ፤

ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበረችው ኢትዮጵያዊቷ/አክሱማዊቷ ንግሥተ ሳባ/አዜብ እስራኤላዊውን ንጉሥ ሰለሞንን ለመጎብኘት ወደ ኢየሩሳሌም በሄደችበት ጊዜ ብዙ አጀብ አስከትላና በርካታ ውድ ገጸ-በረከት/ስጦታን ይዛ ነበር። ከእነዚህ ገጸ-በረከቶች መካከልም፤ ወርቅ፣ ዕንቁ፣ የከበሩ ድንጋዮች፣ ሽቱ፣ ልዩ ልዩ መዓዛ ያላቸው ለሽታና ለግንባታ የሚሆኑ ውብና ጠንካራ እንጨቶች... ይገኙበታል። (መጽሐፈ-ነገሥት ፲፤፲)።

መጽሐፍ ቅዱስ፤ ኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ሳባ ለንጉሥ ሰለሞን ይዛ ስለሄደችው ስጦታ መጠንና ዓይነት ሲናገር፤ ከዛም በፊት ሆነ ከእርሷ በኋላ ለንጉሥ ሰለሞን እንዲህ ዓይነት ስጦታ ተመጥቶለት እንደማያውቅ በአድናቆት ተጽፎአል። እንግሊዛዊው የታሪክና፣ የፖለቲካ ምሁር/ጸሐፊ ዊሊያም ባጅ ደግሞ ከዛሬ 50 ዓመት በፊት፤ "Queen Sheba and Her Only Son Menilik" በሚል ርእስ በጻፈው የዳጎሰ መጽሐፉ፤

" ንግሥተ ሳባ ለንጉሥ ሰለሞን ይዛ የሄደችውን የስጦታ መጠን በዘመኑ የዋጋ ስሌት መጠን 25 ሚሊዮን ፓውንድ እንደሚገመት፤" ጽፏል። ይሄ ስሌት ከዛሬ 50 ዓመት በፊት መሆኑን ልብ ይሏል። በዛሬው የዋጋ ጣሪያና የፓውንድ ምንዛሬ ስናሰላው የሀገራችንን የዓመት በጀት በእጥፍ የሚያስከነዳ ይሆናል። እንግዲህ በዘመኑ ኢትዮጵያውያን/አክሱማውያን ምን ያህል ሀብታምና ታላቅ እንደነበሩና ዛሬ ግን የት እንዳለን ቆም ብለን ማሰብ ነው።

በሌላ በኩልም፤ እንደዛሬው ጠበን ጠበን በጎሳና በጎጥ ተከፋፍለን...የእናንተና የእኛ መሬት እያልን በመገዳደል የዓለም መሳለቂያ ከመሆናችን በፊት የቀደሙት ኢትዮጵያውያን/አክሱማውያን ሰውን በሰውነቱ ብቻ የሚያከብሩ ታላቅ ሕዝቦች ነበሩ። አሁንም ዳግመኛ ዓለም ካወቀው፤ ጸሐይ ከሞቀው ታሪካችን እንምዘዛ፤

በዛን ዘመን የነበሩትኢትዮጵያውያን/አክሱማውያን፤ የነቢዩ መሐመድን ተከታዮች/ሱሃባዎችን በምድራቸው በሰላም ተቀብለው ሲያስተናግዱ፤ ከግሪክና ከሮም ተሰደው የመጡ ተሰዓቱ/፱ኙን መነኮሳት/ቅዱሳንን በግዛታቸው በፍቅር ተቀብለው ሲያስጠልሉ፤ ግብፃውያኑን አባት አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን የሃይማኖታቸው ሐዋርያ ሲያደርጓቸው፤ የኦሮሞ ሕዝብም እኚህን ቅዱስ አባት አቡዬ/አባታችን በማለት በፍቅር ቃል ሲጠሯቸውና ሲያከብሯቸው መለኪያቸው ዘር/ጎሳ/ብሔር ሳይሆን ፍቅር፤ ሰውነት/ሰው መሆን ብቻ ነበር።

እንግዲህ መስቀሉ የፍቅር፣ የአንድነት፣ የሰላም ምልክትም አይደል... ታዲያ ጥንታውያኑ ኢትዮጵያውያን ቅዱስ መስቀሉን በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባር ጭምር የዘከረ እንዲህ ዓይነቱን አኩሪ ታሪክ ትተውልን አልፈዋል።

ወደቀደመው የመስቀል ጥንተ ታሪክ ጉዳይ ስንመለስም፤ አክሱማውያን ክርስትናን ከተቀበሉ በኋላ ከግሪክ አማልክት ወደ ክርስትና ፊታቸውን በመመለስ መስቀልን ምልክታቸው ኢየሱስ ክርስቶስን ደግሞ አምላካቸው አደረጉ። ነገሥታቱ በዘመቱበት የጦር ግንባር ድል ባደረጉበት ጊዜ ሁሉ፤ "በመስቀል ምልክት፤ በአምላካቸውና በጌታቸው በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ድል ማድረጋቸውን!!" የሚዘክር የድንጋይ ላይ ጽሑፍን አስቀርተውልናል። ከእነዚህም መካከል፤

ታዋቂዎቹን "የኢዛና ኢንስክሪፕሽን እና የአዶሊስ ኢንስክሪፕሽንን" የድል ዜናን የሚዘክሩት በግሪክ፣ በግዕዝና በሳባውያን ቋንቋዎች የተጻፉት የአክሱም ነገሥታት የድንጋይ ላይ ሐውልቶች ሺሕ ዘመናት የተሻገረውን ታሪካችንን ለዓለም እየተናገሩ ሕያው ምስክር ሆነው በታሪካዊቷና በጥንታዊቷ የአክሱም ከተማ ዛሬም ድረስ ቆመው ይታያሉ።

በዚህ ታሪካችን ላይ ተጨማሪ ለማወቅ/ለማንበብ ለምትሹ ማስረጃ ላጣቅስ፤

ከ120 ዓመታት በፊት የጀርመንን የታሪክና የአርኪዮሎጂ የጥናት ቡድንን በመምራት በዳግማዊ ዐጤ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ የመጡትና የአክሱምን ታሪክ ለዓለም ያስተዋወቁት፤ የ Deutsche Aksum Expidition የታሪክና የአርኪዮሎጂ ጥናት ቡድን ከሆኑት ውስጥ፤ the Leading Orientalist Eno Litmman, Architect Daniel Krencker, Photographer and Draughtsman Thedor von Lupke and Physician Erich Kaschke በአክሱም ከተማ ባደረጉት የአርኪዮሎጂ ጥናት በቁፋሮ የመስቀል ምልክት የተቀረጸባቸውን የወርቅ ሳንቲሞችን አግኝተዋል። እነዚህ የታሪካችን ሕያው ምስክሮች የሆኑ ሳንቲሞች በታላቅ ክብር- ልዩ ቅርስ ሆነው በብሔራዊ ሙዚየም እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ኢትኖግራፊክ ቤተመዘክር/ሙዚየም ይገኛሉ።

ከአክሱማውያን በኋላ የመጡ ኢትዮጵያውያን ነገሥታት መስቀልን ይጠቀሙ እንደነበርም በርካታ የታሪክ ማስረጃዎች አሉን። የቀደምት ነገሥታት ማኅተም በመስቀል ቅርጽ ሆኖ በአራቱ ማዕዘን ‹‹ኢየሱስ›› የሚል ስም ይጻፍበት ነበረ፡፡ ከዘመነ መሣፍንት ታላላቅ መሪዎች መካከል ሣህለሥላሴ መስቀልን ምልክት ያደርጉ ነበር፤ በመእዘናቱ ኢየሱስ፣ አንዳንዴም ኢየሱስ ክርስቶስ እያሉ ጽፈውበታል፡፡ ከአክሱም ዘመነ መንግሥት የአንደኛው ንጉሣችን ስም ገብረ መስቀል ነበረ፡፡ የላሊበላ ሚስት ስም መስቀል ክብራ ነው፡፡ የዐፄ ይስሐቅ ስመ መንግሥትም ገብረ መስቀል ነው፡፡

ከላይ በመግቢያዬ እንደጠቀስኩት፤ መስቀል በኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ትልቅ ክብር፤ ልዩ ስፍራ አለው። ማንኛውም ሕንጻ ቤ/ክ ያለ ሞገሰ መስቀል አይሠራም። ስግደትና አስተብርኮም ይቀርብለታል። መስቀልን መሳለምና በመስቀል ማማተብ፤ መባረክም የቆየ የቤተክርስቲያን ሃይማኖታዊ ሥርዓት ነው።

መስቀልን በአንገት ማሰር፣ በግንባርና በክንድ ላይ መነቀስ፣ በአልባሳት፣ በአክሊል፣ በዘውድ፣ በገንዘብና በበትረ መንግሥት ላይ የሚደረገው የመስቀል ሃይማኖታዊ ምልክት እንጂ ጌጥ አይደለም።

እንደ ቤተክርስቲያን ሥርዓት ለቅዱስ መስቀል አብያተ ክርስቲያናት ታንጸዋል። ከመስከረም ፲፫ እስከ ፳፫ ያለው ጊዜም ዘመነ-መስቀል ይባላል። በዚህ ወቅት ነገረ መስቀል ይነገራል፤ መዝሙረ መስቀል ይዘመራል። በአጠቃላይ መስቀል በኢትዮጵያ ቤ/ክ የጸሎት ጥንትና ተፍጻሜት ነው።

በመጨረሻም፤ ንጉሠ ሣሕለሥላሴ ከ200 ዓመት በፊት በኢየሩሳሌም ስላለው የኢትዮጵያ ቤ/ክ ገዳም - ስለዴር ሱልጣን ጉዳይ ለእንግሊዛዊው ቆንሲል ሳሙኤል ጎባት የጻፉትን ደብዳቤ ስንመለከት የራስጌ ማሕተማቸው የመስቀል ምልክት እንደነበር ይታያል። ይህን ጥንታዊ ደብዳቤ ከዚህ ጽሑፍ ጋር አባሪ አድርጌያለሁ።

**ታሳቁ ቅዱስ መጽሐፍ፤**

"እግዚአብሔርም በእርሱ፥ በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ጥልንም/ጥላቻንም በመስቀሉ ገድሎ፤ በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአልና፤" እንዲል የአባቶቻችን አምላክ በኢትዮጵያ ምድር ጥልና ጥላቻ/ጠላትነት ተወግዶ የሰላምን ዘመን ምናይበትን ጊዜ ያቅርብልን!! አሜን!!

ዜና

# ‹‹የመከላከያ ሠራዊት ግዳጅ አፈፃፀም አቅምን ለመገንባት ዘርፈ ብዙ ሥራዎችን እየሠራን እንገኛለን››

-ሌተናል ጄኔራል ይመር መኮንን
የመከላከያ ትምህርትና ሥልጠና ዋና መምሪያ ኃላፊ

**ቃልኪዳን አሳዬ**



ፎቶ፡- ገባቦ ገብሬ

አዲስ አበባ፡- የመከላከያ ሠራዊት ግዳጅ አፈፃፀም አቅምን ለመገንባት ዘርፈ ብዙ ሥራዎች እንደ ተቋም በመሥራት ላይ እንገኛለን ሲሉ የመከላከያ ትምህርትና ሥልጠና ዋና መምሪያ ኃላፊ ሌተናል ጄኔራል ይመር መኮንን ገለጹ፡፡

በመከላከያ ትምህርትና ሥልጠና ዋና መምሪያ የውጊያ ምህንድስና ኮሌጅ በተዋጊ መሃንዲስ አመራርነትና በተዋጊ መሃንዲስ መሠረታዊ ሙያ ያሠለጠናቸውን ሠልጣኞችን ትናንት አስመርቋል።

በምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ላይ በመገኘት የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክት ያስተላለፉት የመከላከያ ትምህርትና ሥልጠና ዋና መመሪያ ኃላፊ ሌተናል ጀነራል ይመር መኮንን እንደተናገሩት፤ የመከላከያ ሠራዊት ግዳጅ አፈፃፀም አቅምን ለማሳደግና ለመገንባት ዘርፈ ብዙ ሥራዎች እንደተቋም በመሥራት ላይ እንገኛለን።የሠራዊቱን ግዳጅ አፈፃፀም በየዘርፉ ወደላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ባሳለፍነው ዓመት በሁሉም የሥልጠና ተቋማት የተሳኩ ውጤቶችን ማግኘት ተችሏል፡፡

የተዋጊ አመራር የውጊያ ድጋፍና የአገልግሎት ድጋፍ ሰጪ ሥልጠናዎች በተሳካ ሁኔታ በማጠናቀቅ የሠራዊቱን የውጊያ ዝግጁነት አቅም በእጅጉ ማጠናከር የተቻለ መሆኑን የገለጹት የመምሪያ ኃላፊው፤ የዘንድሮ ተመራቂዎችም የዚሁ አካል መሆናቸውን ጠቁመዋል።

የመከላከያ ሠራዊት ዋና ተልዕኮ ከውጭም ሆነ ከውስጥ የሚቃጡ ጥቃቶችን በመከላከል የሀገርን ሉዓላዊነትና አንድነት እንዲሁም የዜጎችን ሰላምና ደህንነት ማረጋገጥ መሆኑን ለአፍታም እንኳን የምንዘነጋው ጉዳይ አይደለም ብለዋል፡፡

ሠራዊቱ ከሕገመንግሥታዊ ተልዕኮው በመነሳት የህዝቡን ደህንነት ለማረጋገጥ ሲባል ህዝባዊነቱን ጠብቆ ዛሬም እንደ ትናንቱ ግዳጁን በብቃት በመወጣት ላይ ይገኛል ነው ያሉት፡፡

እንደ ሌተናል ጀነራል ይመር ገለጻ፤ የኢትዮጵያን አንድነትና ሉዓላዊነት የማይፈልጉ ተላላኪ ኃይሎች አኩሪ መስዋዕትነትን እየከፈለ ሀገርን ከብተናና ከውድመት እየታደገ ያለውን ሀገር ወዳድ ሠራዊት የተለያዩ ስያሜዎችን እየሰጡ አኩሪ መስዋዕትነቱን ጥላሸት እየቀቡት ቢገኙም ሠራዊቱ ከመቼውም በላይ ዝግጁ በመሆንና እራሱን በማብቃት የተሰጠውን ህዝባዊ አደራ በአስተማማኝ ሁኔታ እየተወጣ ይገኛል፡፡

ሠልጣኞችም በሠለጠኑበት ሙያ የሀገርን ሉዓላዊነትና አንድነት እንዲሁም የህዝቦችን ደህንነት በመጠበቅ የተጣለባቸውን ኃላፊነት በብቃት ሊወጡ እንደሚገባ ሌተናል ጀነራል ይመር አሳስበዋል።

የውጊያ ምህንድስና ኮሌጁ አዛዥ ኮሎኔል ኪታባ እንሴርሞ በበኩላቸው እንደገለፁት፤ ሠልጣኞቹ ባለፉት አራት ወራት በቀንና በማታ ተገቢውን ወታደራዊ ሥልጠና መውሰድ ችለዋል። ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የመከላከያ ሠራዊቱን የመፈፀምና የማድረግ ሁለንተናዊ ክህሎት በማሳደግ ብቃት ያላቸውን አመራሮችን ለማፍራትና የወቅቱ ውትድርና የሚፈልገውን የቴክኖሎጂ እውቀት ለማስጨበጥ ሚናቸው የጎላ መሆኑን ሠልጣኞች ማሳያ ናቸው።

የውጊያ ምህድስና ኮሌጅም ብቃት ያላቸው ሙያተኞችና ሙያውን የሚያውቁ አመራሮችን በማፍራት የተቋሙን የሠለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት የማሟላት ተልዕኮውን ለማሳካት ጠንክሮ በመሥራት የበኩሉን የማይተካ ሚና እየተጫወተ እንደሚገኝ ኮሎኔል ኪታባ ጠቁመዋል፡፡

ተመራቂዎቹ አስተማማኝ የውጊያ ድጋፍ መስጠት የሚችሉ የውጊያ መሀንዲስ አመራሮችና ሙያተኞች መሆናቸውን ተናግረዋል።

በመከላከያ ትምህርትና ሥልጠና ዋና መምሪያ የውጊያ ምህንድስና ኮሌጅ በ1934 ዓ.ም የተቋቋመ ሲሆን በአምስት የትምህርት መስኮች የተለያዩ ወታደራዊ ሥልጠናዎችን በመስጠት ላይ እንደሚገኝ ታውቋል፡፡

# ኢትዮጵያ ከብሪክስ ተገቢውን ጥቅም ለማግኘት የሚጠበቁባት ዝግጅቶች

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ከብሪክስ ተገቢውን ጥቅም እንድታገኝ ውስጣዊ ሠላም ማስጠበቅ፣ ቢሮክራሲን ማስቀረትና ሙስናን መዋጋትን ጨምሮ ለትብብር እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮች ላይ ተገቢውን ዝግጅት ማድረግ እንዳለባት የምጣኔ ሀብት መምህሩ ገለጹ፡፡

በሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህሩ ረዳት ፕሮፌሰር ሀብታሙ ለገሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ብዙዎቹ የብሪክስ አባል ሀገራት በቴክኖሎጂና በኢኮኖሚ ትልቅ አቅም የፈጠሩ በመሆናቸው ኢትዮጵያ ይህን ጥምረት መቀላቀሏ ንግድና ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ትልቅ እድል ይፈጥርላታል።ከጥምረቱ ተገቢውን ጥቅም እንደታገኝ ግን አስተማማኝ ሠላም ማስፈን፣ ቢሮክራሲን ማሳጠር፣ ሙስናን መዋጋትን ጨምሮ ከሌሎች ሀገራት ጋር በትብብር ለመሥራት እንቅፋት ሊፈጥሩ የሚችሉ ጉዳዮችን ለይቶ የእርምት ርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል ይላሉ፡፡

ቀደም ሲል የብሪክስ አባል ሀገራት የነበሩት ብራዚል፣ ሩስያ፣ ህንድ፣ ቻይናና ደቡብ አፍሪካ ከዓለም ሕዝብ 42 በመቶ የሚደርሰውን ይሸፍኑ እንደነበር ያስታወሱት ምሁሩ፤ ጥያቄያቸው ተቀባይነት ያገኙትን አምስቱ ሀገራት ሲጨምር ድርሻቸው ወደ 47 በመቶ ከፍ ብሏል።ከዓለም ኢኮኖሚው የነበራቸው ድርሻም ከነበረበት 26 በመቶ ወደ 30 ተጠግቷል።ኢትዮጵያ ከዓለም ሕዝብ ግማሽ የሚጠጋውን ቁጥርና ከፍተኛ የኢኮኖሚ ድርሻ ካለው ብሪክስ ውስጥ መግባቷ ብዙ እድሎችን ይዞ ይመጣል።

እንደ ረዳት ፕሮፌሰር ሀብታሙ ገለጻ፤ የብሪክስ አባል ሀገራት የዓለም ባንክ አማራጭ ሆኖ የመጣው ኒው ዴቨሎፕመንት ባንክ የሚባልና በዋናነት መሠረተ ልማት እንዲሁም ቀጣይነት ያላቸው የልማት ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ የሚያደርግ ባንክ አላቸው። ባንኩ እስካሁን ድረስ 90 የሚደርሱ ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ አድርጓል። ይህም ጥሩ የፋይናንስ ምንጭና መደራደሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡

አሁን ላይ የአባልነት ጥያቄያቸው ተቀባይነት ያገኙ ሀገራትም ጠንካራ ሀገራት በመሆናቸው ስብስቡ በዓለም ኢኮኖሚና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖና ተሰሚነት ከፍ እንደሚያደርገው ጠቅሰው፤ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በማሳደግና ንግድ በመስፋፋት በኩል ትልቅ እድል ይፈጥራል ነው ያሉት።

ኢትዮጵያም ያላት የሕዝብ ብዛት፣ የቆዳ ስፋቷና ያላት ሀብትና የገበያ ፍላጎት ጥያቄዋ ተቀባይነት እንዲያገኝ ትልቅ ሚና እንዳለው አመላክተው፤ የብሪክስ አባል ሀገራት የምዕራባውያንን ተጽዕኖ በተለይም የዶላርን የበላይነት ለመቀነስ አዲስ የመገበያያ ገንዘብ ለመመስረት ብሎም በየሀገራቱ ገንዘብ ለመገበያየት አቅደዋል።ይህም የውጭ ምንዛሪ ችግርን ለመቅረፍ ያግዛል የሚል ሃሳባቸውን ሰጥተዋል፡፡

ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል መሆኗ ብቻ ተጠቃሚ ስለማያደርጋት ከጥምረቱ ተገቢውን ጥቅም ለማግኘት መሥራት ያለባትን የቤት ሥራዎች ከወዲሁ ማከናወን አለባት ብለዋል።

የብሪክስ አባል ሀገር ስለሆን ብቻ ከዓለም ባንክ፣ ከዓለም አቀፉ ገንዘብ ድርጅትና ከአሜሪካ የምናገኘው ድጋፍ ይቆማል ግንኙነታችንም ይቋረጣል ማለት እንዳልሆነ ጠቁመው፤ እንደ ሀገር ብዙ የሀብት እገዛ ስለሚያስፈልገን በውስጣዊ ጉዳያችን ጣልቃ እስካልገቡ ድረስ ከየትኛውም ወገን የምንናገኘውን እድል በአግባቡ መጠቀም ይኖርብናል ሲሉ ይገልጻሉ።

ቻይናና ደቡብ አፍሪካ እንደሚያደርጉት በብልጠት ከሁለቱም ወገን ጋር ያለንን ግንኙነት ማስቀጠል አስፈላጊ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

በደቡብ አፍሪካ ጆሀንስበርግ ከተማ በተካሄደው 15ኛው የብሪክስ አባል ሀገራት የመሪዎች ጉባዔ ጥምረቱን ለመቀላቀል ጥያቄ ካቀረቡ ከ40 በላይ ሀገራት መካከል ኢትዮጵያን፣ አርጀንቲና፣ ግብጽ፣ ኢራን፣ ሳዑዲ አረቢያን እና የተባበሩት አረብ ኢሚሬቶችን ከመጪው የፈረንጆቹ ጥር አንድ ቀን 2024 ጀምሮ በአባልነት መቀበሉ ይታወሳል፡፡

# “የእኛ ፍላጎት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ድል በድል፣ ሥራ በሥራ፣ ውጤት በውጤት፣ ስኬት በስኬት፣ መከናወን፣ በመከናወን እና መጽናት በመጽናት ይቀጥላል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በኢትዮጵያ ይበልጥ ሊሠራባቸውና ለቱሪዝም መስህብ ሊሆኑ የሚችሉ በርካታ ቦታዎች አሉ። ቦታዎቹ ላይ ጥቂት የሰዎች ሥራ ቢታከልበት ለብዙ ኢትዮጵያውያን ኩራት፣ የሥራ እድልና መዝናኛ እንደሚሆኑ ገልጸዋል።

የጅማ ከተማ በአዲሱ ገበታ ለትውልድ ከተመረጡ ቦታዎች ውስጥ አንዱ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ይህ ቦታ ከሁለትና ሦስት ዓመት በኋላ እጅግ የሚያምር ስፍራ ይሆናል። የጅማ ገበታ ለትውልድ ፕሮጀክት የከተማውን ገጽታና የአኗኗር ዘይቤ በእጅጉ እንደሚለውጥ ተናግረዋል።

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለፃ፤ የጅማ ከተማ ከአዲስ አበባ በአንድ ሺህ አምስት መቶ ሜትር ከፍታ ዝቅ ያለ ነው። ዝቅ ማለቱ የሙቀት መጠኑን ከፍ ያደርገዋል። ይህም በአካባቢው የሚተከሉ እጽዋቶች ቶሎ እንዲበቅሉ ያደርጋል። ይህን ዕድል በመጠቀም የጅማ ከተማ ነዋሪዎች የእንጨት ሙያቸውንና የተፈጥሮን ስጦታ በማጣመር የአካባቢውን ገጽታ ይበልጥ ማስዋብ ይኖርባቸዋል።

ከተማ የማስዋብ ሥራ ቀላል የሚባል አይደለም አድካሚና አታካች ሥራ ነው። አታካችና አድካሚ ያልሆነ ሥራ ደግሞ ውብት የለውም። የጅማ ልጆች መልካም፣ ውብና ያማረ ቦታ ማየት፣ ማለምና መሥራት እንዲችሉ ነዋሪዎች ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንዳለባቸው ተናግረዋል።

ሚዛን አማን ላይ የሚሠራው አዲስ ሪዞርትና ኮይሻ አካባቢ የሚሠራው ፕሮጀክት ከጅማ ከተማ በቅርብ ርቀት የሚገኙ ናቸው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ እነዚህን ማገናኘት ቢቻል አጠቃላይ ምዕራብ ኢትዮጵያ ለብዙ ሰዎች የሳምንትና የአሥራ አምስት ቀን ማረፊያና መዝናኛ ቦታ መሆን የሚችል ነው ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህንን ለማድረግ ልብን ሰብሰብ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ገልጸው፤ ብዙ ሊሠራ የሚገባው ሥራ አለ። ነገር ግን ቆርጦ በመሥራት ለውጥ ማምጣት እንደሚገባ ገልጸዋል።

የሰው ልጅ ለምግብ ፍጆታ የሚሆነውን በቅርበት ማግኘት የሚችል ከሆነ ውብና ማራኪ ቦታዎች ሊኖሩት ይገባል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ውበትን የምናይበት፣ የምንሠራበትና የምናደንቅበት መንገድ የእኛን ልክ የሚገልጥና የሚያሳይ ነው ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ዓርብ መስከረም 18 ቀን 2016 ዓ.ም በጅማ ከተማ ማምሻውን ከተማዋን በእግር ጎብኝተዋል።

# በመዲናዋ በቀን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከከርሰምድርና ከገፀምድር ውሃ ለማልማት አቅጣጫ ተቀምጦ በተከናወነው ሥራ በቀን 792ሺ ሜትሪክ ኪዩብ ውሃ የማምረት አቅም መፍጠር ተችሏል፡፡

አዳዲስ ግንባታዎችን በተመለከተም አቶ ፍቃዱ እንደገለጹት፤ ሱሉልታ አካባቢ ገርቢ ግድብን ለመሥራት የጥናት፣ ወሰን የማስከበር፣ ቴክኒካል ሥራዎች፣ ኮንትራክተር የመምረጥና ሌሎችም የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች መጠናቀቃቸውንና የግድቡ ግንባታም የሚከናወነው ከቻይና መንግሥት በሚገኝ የገንዘብ ብድር እንደሆነ አስታውቀዋል፡፡

ብድሩ እንደተለቀቀ ወደ ሥራ እንደሚገባ የገለጹት አቶ ፍቃዱ፤ ይህ ፕሮጀክት የቆየ መሆኑንና በወቅቱ የሶስት ዓመት ፕሮጀክት ተብሎ መያዙንም ጠቁመዋል።በወቅቱም ለሥራው የተቀመጠው የገንዘብ መጠን ወደ 95 ሚሊዮን ዶላር አካባቢ እንደሆነና ከግድቡ ሥፍራ ወደ አዲስ አበባ ከተማ የሚመጣው ውሃ በበላይ ዘለቀ አድርጎ ድል በር አካባቢ ላይ የመጀመሪያውን ማጠራቀሚያ በማለፍ ሽሮሜዳ፣ ቀጨኔ እና ጉለሌ አካባቢን በከፊል ተጠቃሚ እንደሚያደርግ አስረድተዋል፡፡

በዋናነት በስተሰሜን ያለውን አዲስ አበባ ከተማ በከፍተኛ ደረጃ ያለውን የውሃ አገልግሎት አቅርቦት ችግር ለመፍታት የሚያስችል እንደሆነ ገልጸው፤ እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ የውሃ አቅርቦት ላይ የተሰጠው ትኩረት አንዱ ማሳያ እንደሆነም አመልክተዋል፡፡

በድምሩ ከ2011 እስከ 2015 ዓ.ም ባሉት ዓመታት ከ275 ሺ ሜትር ኪዩቢክ ተጨማሪ ውሃ ወደ ከተማዋ እንዲገባ መደረጉን የጠቆሙት አቶ ፍቃዱ፤ በየአመቱ ሥራ እየተሠራ ተጨማሪ ውሃ ወደ ከተማዋ እንዲገባ ቢደረግም የከተማው የውሃ ፍላጎት ሊጣጣም እንዳልቻለ ጠቅሰዋል፡፡

እንደ አቶ ፍቃዱ ማብራሪያ፤ ለመኖሪያም ሆነ ለተለያየ አገልግሎት እየተከናወነ ያለው ግንባታ ወደ ላይ ወይንም ፎቅ መሆኑ በውሃ አቅርቦትና በፍላጎት መካከል ክፍተት እንዲፈጠር የራሱ አስተዋጽኦ አድርጓል።የመሬት አቀማመጡም በራሱ ተግዳሮት ፈጥሯል።ለውሃ መገኛ ቅርብ የሆኑና በአቀማመጣቸውም ምቹ የሆኑ አካባቢዎች ብቻ ውሃ የሚያገኙበት፣ ምቹ ባለመሆናቸው፣ ኢንዱስትሪዎች፣ ሆስፒታሎችና ትላልቅ የሚባሉ ፕሮጀክቶች በስፋት በአካባቢው መኖራቸው ውሃ የማያገኙበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው፡፡

እንደ አቶ ፍቃዱ ገለጻ፤ እንዲህ ያለውን ችግር ለመፍታት እንደ ውሃ መገኛ ሁኔታ የፈረቃ ሥርዓት በመዘርጋት ሁሉም በተራ አገልግሎቱን እንዲያገኝ እየተደረገ ነው። ህብረተሰቡም በሥርዓት ውስጥ ገብቶ በአገልግሎቱ ተጠቃሚ የመሆን ዝግጁነቱን አሳይቷል።አሁን ላይ ከህብረተሰቡ እየተነሳ ያለው ከአካባቢ አካባቢ ልዩነት ለምን ተፈጠረ የሚል በፈረቃ አገልግሎት ፍትሐዊነት ላይ ነው፡፡

ለከተማው የሚሰራጨው ውሃ ሁሉም ከአንድ ቋት ውስጥ እንዳልሆነ ግንዛቤ መያዝ እንዳለበት የጠቆሙት አቶ ፍቃዱ፤ ውሃ ወደተለያየ አካባቢ ለማሰራጨት ጥረት ሲደረግ በተለያየ የአሠራር ዘዴ ወይንም ሲስተም እንደሆነም ገልጸዋል።

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ባህላዊ ወረቶቻችንን ለአብሮነትና ለአንድነት፤

ዶ/ር ጆሴፍ ጎብልስ የናዚው አዶልፍ ሒትለር የአስገድዶ የማሳመንና የማጥመቅ ወይም ኢንዶክትሬሽን አልያም የፕሮፓጋንዳ ቀኝ እጅ ሲሆን ውሸት ሲደጋገም እውነት ይሆናል ይል ነበር። እኛ ግን አይደለም ውሸትን ደጋግሞ በመንገር እውነት ማድረግ እውነቶቻችንንም እውነት ማድረግ ተስኖናል። የታቀፍናቸው ቱባ በባህላዊ ወረቶቻችን በሦስቱ አብርሃማዊ እምነቶች ማለትም በክርስትና፣ በይሁዲና በእስልምና በትውልድ ቅብብሎሽ የታሹ፣ የተፈተኑና የተረጋገጡ እውነቶች ቢሆኑም እውነት ማድረግ፣ መኖር፣ በሕይወታችን መግለጥ ተስኖን በሀገራችን ልዩነት፣ መጠራጠር፣ መፈራረጅና መከፋፈል ሠልጥኗል። ለባህላዊ ወረቶቻችንን ዋጋ ያልሰጠነው፣ ትኩረት የነፈግነው፣ ኬሬዳሽ የሆነው ደጋግመን በማንሳት ከፍ ሲልም ሀገርንም ሕዝብንም ሌት ተቀን በመነዝነዝ ቀዳሚ አጀንዳ ማድረግ ባለመቻላችን ነው።

እነዚህ ወረቶቻችንን የመነጋገሪያ «አንገብጋቢ ጉዳይ» ወይም “Issue Salience” ብናደርጋቸው ኑሮ ዛሬ ሀገራችን የምትገኝባቸውን ቋጠሮች ሁሉ በፈታቱልን። እነዚህን የእርቅ ፣ የአብሮነት፣ የአንድነት፣ የይቅርባይነትና የሰላም ወረቶች በእጅ የያዙት ወርቅ እንደ መዳብ ይቆጠራል እንዲሉ። ለሀገራዊ ምክክር ከእነዚህ ወረቶቻችን ቀምረን አማካኝ መላ ይዘን መምጣት እየቻልን ለቅልውጥ ደቡብ አፍሪካና ሩዋንዳ ባልዘለቅን። በዚህ ጋዜጣ ላይ ደጋግሜ እንደ ዝሀ ዘጊ የምመላለስበት የባህላዊ ወረቶቻችን ወይም ማኀበራዊ ወረቶቻችን ካልቸራል/ሶሻል ካፒታልስ ጉዳይ ምን አልባት አንድ ቀን ለአቅመ አጀንዳ ይበቃል በሚል ተላላነት ነውና ። ባህላዊ ወረቶቻችን በብዛት በመላው ሀገራችን በብዛት በሚገለጡበት በዚህ ወር እንደገና ይዤው ተመልሻለሁ።

ወርሃ መስከረም በርካታ ሃይማኖታዊና ባህላዊ በዓሎች የሚከወንበት ባለደማቅ ቀለማትና ህብራዊ ወር ነው። ተፈጥሮም ኢትዮጵያውያንም የሚያጌጡበት ሽቅርቅር ወር ነው። ባህላዊ ወረቶቻችን Cultural Capitals በርከት ብለው የሚገኙበት ባለጸጋ ወር ነው። ሆኖም በሌሎች ወራትም እንደ መስከረም ሁሉ ከፍ ያሉ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ወረቶች ቢኖሩም በዕለት ተዕለት ኑሮአችን እየገለጥናቸው፣ እየኖርናቸው፣ እየተረጎምናቸው እየወጣን እየገባንባቸው ስላልሆነ እና ላለፉት 50 አመታት ልዩነት፣ ጥላቻ፣ ጎሰኝነትና የፈጠራ ትርክት ተቋማዊና መዋቀራዊ ሆነው ስለተለፈፉ፤ እዚህም እዚያም ቀውስ ፣ ነውር ለማመን የሚቸግሩ ጭካኔዎችን ፣ ግፎችን ፣ መከፋፈል ፣ መጠራጠር እያስተናገድን ነው ።

በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የተቋቋመው የሚኒስትሮች ግብረ ኃይል ጥልቅ በሆነው ምርመራውና ጥናቱ የደረሰበትን ግኝት ይፋ ተደርጎ የሚዘገንኑ፣ ለመስማት የሚሰቀጥጡ፣ ኢ-ሰብአዊ አረመኔያዊ ግፎችን ስንታዘብ የሦስቱ አብርሃማዊ ሃይማኖቶች ማለትም ክርስትና፣ አይሁድና እስልምና በአንድነት በሚገኙበት ሀገር እንዴት ሊፈጸም ቻለ? ዋቄ ፈና የሚከተል ሕዝብ ባለበት እንዴት እንዲህ ሊሆን ቻለ? ብለን ስንጠይቅ መልሱ ባህላዊ ወረቶቻችን በአግባቡ አልምተን ስላልተጠቀምንባቸው ነው።

ለመሆኑ ባህል፣ ባህላዊ ንብረትስ ምንድን ነው የሚለውን ለመግባቢያ ያህል እንመለከት። ባህል ሁሉንም የሚያስማማ የሚያግባባ ወጥ የሆነ ትርጉም ብያኔ ባይኖረውም የአንድ ማኅብረሰብ ወይም ሕዝብ እምነት፣ ልማድ ፣ ወግ በኪነ ጥበብ እና በሥነ ጥበብ ተዳውሮ፣ ተሸምኖ፣ ተንሰላስሎ የመገኘት፣ የመገለጥ ዥጉርጉር ኅብራዊ ቀለም ነው። በደስታ፣ በኀዘን፣ በሥራ፣ በሃይማኖት፣ በትምህርት፣ ወዘተ የሕይወት ገጾች ይገለጻል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል የተዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ባህልን፦ የኅብረተሰብ የአኗኗር ዘዴ ፣ ወግ፣ ልማድ ፣ እምነት፣ …። በማለት ሲተረጉመው። የደስታ ተክለ ወልድ የአማርኛ መዝገበ ቃላት በበኩሉ ባህል፦ ልማድ፣ ደንብ ሲል ይፈታዋል።

ባህላዊ ወረት (cultural capital) የሚለው ሐረግ ፔሬ ቦርዴው በተባለ በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ማብቂያ ላይ የተነሳ የሥነ ኅብረተሰብ ተመራማሪ እንደተፈጠረ የተለያዩ የዘርፉ ድርሳናት ያትታሉ። ባህላዊ ወረት በማኅበረሰብ ውስጥ ያለን ተቀባይነት ቦታ ከፍ ለማድረግ እውቀትን፣ ፀባይና ክህሎትን የማሳደግ የማካበት ሂደት ነው። ባህላዊ ንብረት ወይም ወረት በግለሰብ፣ በማኅበረሰብ ከፍ ሲልም በሕዝብ በሀገር ይሰላል። የበለፀገ ባህላዊ ንብረት ያካበተ ግለሰብ በማኅበረሰቡ ዘንድ ያለውን ተቀባይነት ከፍ እንደሚያደርገው ሁሉ ያደገ የለማ ባህላዊ ንብረት ያለው ማኅበረሰብ ሕዝብ በተመሳሳይ ሁኔታ ከፍ ያለ ተቀባይነት ይኖረዋል።

ባህል ማለትም የኅብረተሰብ የአኗኗር ዘዴ፣ ወግ፣ ልማድ፣ እምነት ፣ ወዘተ . በሂደት በእውቀትና በክህሎት እየበለፀገ፣ እየዳበረ ሲሄድ ለሀገር ሰላም ፣ አንድነት ከፍ ሲልም እድገት የላቀ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በተቃራኒው ባህል በእውቀት፣ በክህሎት ካልበለፀገ አይደለም ለሀገር ሰላምና ዕድገት መዋል ይቅርና የማኅበረሰቡን እሴቶች ጠብቆ ማቆየት ካለማስቻሉ ባሻገር የዕለት ተዕለት ችግሮችን እንኳ መፍታት የሚሳነው ይሆናል። ባህላዊ ንብረት እንደ ኢኮኖሚያዊ ንብረት ማለትም ገንዘብ በአግባቡ ኢንቨስት ተደርጎ ሰላምን፣ ፍቅርን፣ እርቅን፣ መነጋገርን ፣ መቀባበልን፣ መከባበርን ፣ መተባበርን፣ አንድነትን ፣ ወዘተ . እውን ማድረግ ካልቻለ እንደባከነ እንደከሰረ ሊቆጠር ይችላል።

ሀገርን ሕዝብን ከግጭት፣ ከቀውስ፣ ከመፈናቀል፣ ከመጠራጠር፣ ከጥላቻ ፣ ከበቀል ፣ ወዘተ . መታደግ አልቻለማ። እስኪ ለአንድ አፍታ ባህሎቻችንን እምነቶቻችንን ወይም ባህላዊ ንብረቶቻችንን ከዚህ አኳይ እንመዝናቸው። ባክነዋል ወይስ በአግባቡ ሥራ ላይ ውለዋል!? አሁን ከምንገኝበት ሀገራዊ ቁመና አንጻር ባክነዋል ቢባል የሚያስኬድ ይሆናል። ታዲያ እነዚህን ባህላዊ ንብረቶቻችንን እንደ ጦር ዕቃ ለብሶ እንደ ጥሩር ደፍቶ መውጣት መግባት፣ መመላለስ ለምን ተሳነን ? መልሱ ቀላል ነው። ላይ ላዩን እንከውናቸዋለን እንጂ አንኖራቸውም። በቃል እናነበንባቸዋለን እንጂ በልባችን አላተምናቸውም። በዩኔስኮ ለማስመዝገብ እንሯሯጣለን እንጂ በሥርዓተ ትምህርታችን አካተን ትውልድን ለማነጽ አላዋልናቸውም። ለብሔራዊ መግባባት፣ እርቅ፣ አንድነትና ሰላም ካላቸው ፋይዳ ይልቅ ስለሚስቡት ጎብኚና ቱሪስት እንጨነቃለን። ወደ ተራ ሸቀጥ እናወርዳቸዋለን። ይህ የተንሸዋረረ እይታ ሊስተካከል ይገባል።

ባልንጀራህን፣ ጎረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ የሚሉ አብርሃማዊ እምነቶችን ማለትም ክርስትናን፣ እስልምናንና አይሁድን እየተከተልን እንዴት በጥል ግድግዳ ተለያየን!? በአንድ አምላክ በዋቄ ፈና እያመን ኢሬቻን በየአመቱ እያከበርን እየከወን ይቅር መባባል ለምን ተሳነን? መልሱን ለማግኘት ምስጢሩን ለማወቅ ሞራ ማስገለጥ ወይም ኮከብ ማስቆጠር አያሻም። መልሱ ቀላል ነው። እሱም ባህላዊ ንብረቶቻችንን በካዝና ቆልፈን አስቀመጥን እንጂ ሥራ ላይ ስላላዋልናቸው (ኢንቨስት) ስላላደረግናቸው ነው። ትልቁን የመደመር ፍልስፍናም ሆነ ሀገራዊ ሠላምና አንድነት እውን ለማድረግ የተቆለፈባቸውን ባህላዊ ንብረቶች ከካዝና አውጥቶ በእያንዳንዱ ዜጋ ላይ በፍጥነት ማፍሰስ ኢንቨስት ማድረግ ይጠይቃል።

በኢኮኖሚክስ አስተምህሮ ባህል ከተፈጥሮ፣ ከሰውና ከአካላዊ ፣ ቁስ አካላዊ (physical) ቀጥሎ 4ኛው ንብረት ሆኖ መጠናት፣ መተንተን ከጀመረ ከራርሟል። በአግባቡ ጥቅም ላይ ከዋለ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለሀገር እድገትና ለዘላቂ ሠላም አስተዋጽኦ ያበረክታል። ሠላም በሌለበት ኢኮኖሚያዊ እድገትም ሆነ ብልፅግና ሊታሰብ አይችልምና። የመደመር ሦስቱን አላባውያን መሰብሰብ፣ ማከማቸትና ማካበትን እውን ማድረግ አይታሰብም።

ለሀገር ግንባታ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ ወሳኝ ሚና ከሚጫወተው ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ሥርዓት በተጨማሪ ለዘመናት እንደ ሕዝብ ፣ እንደ ሀገር አጋምዶ ያቆየን ባህላዊ ንብረታችን ነው። ሁነቱን፣ ከዋኔውን፣ መንፈሱን ጠብቆ ተንከባክቦና አልምቶ ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ፣ ማስቀጠል፣ ማክበርና ማስተዋወቅ ትልቅ ኃላፊነትም አደራም ነው። ሆኖም የመጨረሻ ግብ ሆኖ ግን ሊወሰድ አይገባም። ቱባነቱን እንደጠበቀ ማደግ ዘመንና ትውልድ መዋጀት ይጠበቅበታል። አዎ ! የትውልዱንና የዘመኑን ህፀፅ የሚያርም ለምፅ የሚያነጻ ፣ የሚዋጅና የሚቤዥ መሆን አለበት።

ዘረኝነትን፣ ጥላቻን፣ ቂም በቀልን፣ ደባን፣ መከፋፈልን፣ ወዘተ መቤዥ፣ መዋጀት አለበት። ባህላዊ ንብረታችንን ይበልጥ በማጎልበት፣ በማልማትና በማስፋት ለመጻኢ ዕድላችን፣ ለነገ ተስፋችን፣ ለእርቅ፣ ለሠላም፣ ለአንድነት፣ ለሁለንተናዊ ብልፅግና፣ ለመደመር ወዘተ. ልናውለው ይገባል። ስኬቶቻችንን የምናወድስበት፣ ፈተናዎቻችንን የምንሻገርበት ነገአችንን የምንተልምበት ጭምር አድርጎ ስለመጠቀም አበክረን ማሰብ ያስፈልጋል።

የፍቅር፣ የእርቅ ፣ የሠላም ፣ የአብሮነት ፣ የማካፈል፣ የመተባበር፣ የመተጋገዝ፣ የመረዳዳት፣ የምስጋና፣ ወዘተ ባህሎች፣ ልማዶች ፣ እምነቶች ፣ ሃይማኖቶች ከፍ ሲልም ድምር ባህላዊ ንብረቶች ባለቤት እንዲሁም የጥንታዊት ሀገር ባለቤት ሆነን አንድነትን በመከፋፈል ከሰዋን፣ ፍቅር ከጎደለን፣ እርቅ ከገፋን፣ ሠላም ከራቀን፣ አብሮነትን በቀዬአዊት ከተካን፣ ማካፈልን በስስት ከቀየርን፣ መተባበርን በመለያየት ከለወጥን፣ ምስጋናን በእርግማን ከተካን፣ ወዘተ ምኑን ሙሉኡ ሆነው? ባለፉት ሦስትና አራት ዓመታት ያለፍንባቸው ሀገራዊ ውጣ ውረዶች፣ አሳፋሪ ድርጊቶች እውነት የእነዚህ ሁሉ መንፈሳዊና ባህላዊ ፀጋዎች ባለቤት ስለመሆናችን የሚመሰክሩ ናቸው? እስኪ ሌሎችን አቆይተን ካለፉት 19 ቀናት ወዲህ እንዲሁም ወደፊት በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች የሚከበሩ መንፈሳዊና ባህላዊ ሁነቶች የተሸከሙትን ግዙፍ መልዕክቶችና አንድምታዎች አለፍ አለፍ ብለን እየተመለከትን ሂሳብ እናወራርድ።

ፍቼ ጨምበለላ፣ ቡሔ ፣ ሻደይ ፣ አሸንዳ፣ ሶለል አይነ ዋሬ ፣ እንቁጣጣሽ ፣ መስቀል ፣ መስቀላዮ፣ አጋመ፣ ጊፋታ፣ ኢ ሬቻን ፣ ጋሮ ፣ ቺሜሪ፣ ወዘተ . በአንድም በሌላ በኩል በተለያዩ የሀገራችን ማኅበረሰቦች የሚከበሩ ሃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ ክዋኔዎች ናቸው። ሁሉም ማለት ይቻላል ተስፋን ፣ ፍቅርን ፣ ነፃነትን ፣ አብሮነትን፣ ምስጋናን ፣ እርቅን ፣ ይቅርታን ፣ ወዘተ. የሚያውጁ፣ የሚለፍፉ ናቸው። ግን በነቂስ ወጥተን ለዘመናት በየአመቱ በአደባባይ የምናከብራቸው የምንዘክራቸውን ያህል በዕለት ተዕለት ኑሮአችን አንኖራቸውም። አንለማመዳቸውም።

ከገጠሙን ቀውሶች፣ ፈተናዎች መውጣት ማገገምና ማንሰራራት የቻልነው በቀሩን ሽርፍራፊ እንጥፍጣፊ በባህላዊ ንብረቶቻችን ነው። በተለይ ባለፉት 27 ዓመታት ቀን ከሌት እንደተሰበከው ልዩነት ፣ ጥላቻና ዘርኝነት ቢሆን ኑሮ እርስ በእርስ ተበላልተናል። ተጨራርሰናል። ለዚህ ነው መዳኛችን፣ ማገገሚያችንና ማንሰራሪያችን የሆነውን ባህላዊ ንብረት ወደሙላቱ መመለስ ለነገ የሚባል ጉዳይ የማይሆነው። ባህላዊ ንብረታችን ለበጎ ዓላማ ሲውል ሀገርን ከጥፋት ከእልቂት እሳት እንደሚታደግ በጋሞ ሀገር ሽማግሌዎች ተመልክተናል።

> ባህላዊ ወረት በማኅበረሰብ ውስጥ ያለን ተቀባይነት ቦታ ከፍ ለማድረግ እውቀትን፣ ፀባይና ክህሎትን የማሳደግ የማካበት ሂደት ነው

ቁጣ አብራጁ ይህ የጋሞ አባቶች ልመና (ጋሞ ወጋ) እየጠፋ፣ ትኩረት እየተነፈገው ያለው ባህላዊ ንብረታችን ተጠብቆ ለትውልድ ሲተላለፍ ሀገርን እንዴት ማዳን እንደሚችል ጥሩ ማሳያ ነው። የጋሞ አባቶች የ2011 ዓ.ም ልዩ የበጎ ሰው ተሸላሚ መሆናቸው በሁሉም ኢትዮጵያዊ ዘንድ ያለ አንዳንች ልዩነት ዳር እስከዳር አድናቆትን ተቀባይነትን ያተረፈው በዚህ እሳቤ ነው።

ሠላምን ፣ ፍቅርን ፣ ይቅርታን ለማነፅ ፣ ለመገንባት ከምንሰጠው ትኩረት ባልተናነሰ በየአካባቢው እንደ ጋሞ ወጋ ዓይነት የሽምግልና፣ የእርቅ ባህላዊ ካፒታሎቻችንን ላይም መሥራት ይጠበቅብናል። ከዚህ መሳ ለመሳ የአክራሪነት አዝማሚያ፣ እኩይ አስተሳሰብ እንዲገታ ብሎም ተሸንፎ ከሰላምና ከእርቅ መንገድ ገለል፣ ዘወር እንዲል ድልብ የሆኑ ባህላዊ ንብረቶቻችን ጥንስስ፣ ወረት የማይተካ ሚና አላቸው። ሁሉም ኢትዮጵያውያን የተለያዩ ባህላዊ ንብረቶች ባለፀጋ ስለሆኑ የየራሳቸውን መዋጮ ማበርከትና ወደ ሥራ መግባት ይጠበቅባቸዋል።

በየአካባቢያችን፣ በየቀዬአችን የምናንፀው፣ የምናቀነቅነው ከባቢያዊ ብሔርተኝነት ወደ አክራሪነት፣ ፅንፈኝነት የሚያንደረድር ወደገደል አፋፍ የሚገፋ ስለሆነ እነዚህን ባህላዊ ወረቶች በመጠቀም መግታት ያስፈልጋል። የዜጎች ማንነት እሴት እንደተከበረ ወደ ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት የሚያደርሰንን ቀና መንገድ በቅንነት መቀላቀል ፣ መያያዝ ይገባል። ይህ ሀገራዊ ብሔርተኝነትም ከገደቡ ፣ ከውሃ ልኩ እንዳያልፍ ጥንቃቄ ማድረጉ እንዳለ ሆኖ። አይደለም ዘውጌአዊ፣ ወንዜአዊ ብሔርተኝነት ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት በአግባቡ ካልተያዘ ፤ የጎረቤቱን የሚጎመጅ ፣ የሚመኝ፣ የሚመቀኝ ሆኖ የመውጣት አደጋ ስላለው በብልሀት ፣ በማስተዋል ሊቀነቀን ይገባል ።

**ሻሉም !!! አሜን ።**

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# ከየኔታ እስከ ዋቄ ፈታ

**እፀገነት አክሊሉ**

መምህር ዮሐንስ ሺበሺ የተወለዱት ከሰላሌ በቅርብ ርቀት በሚገኘው ምሥራቅ ጎጃም ደጀን ከተማ ሲሆን እድገታቸውም እዚያው ነበር ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስም በአካባቢያቸው በአብነት ትምህርት ቤት ፊደል መቁጠር ጀመሩ፡፡ በዚያ የልጅነት ዕድሜያቸው ቀለም የመቀበል ችሎታቸው እጅግ የላቀ የነበረ ሲሆን በመምህራኖቻቸውም ላቅ ያለ ፍቅር ነበራቸው፡፡ በትምህርት አቀባበላቸው በጣም ፈጣን ስለሆኑም ቅኔ እና ዜማ በአጭር ጊዜ ውስጥ አቀላጥፈው ተማሩ።

መምህር ዮሐንስ የዜማ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ በቀጥታ የሄዱት ወደቅኔ ቤት ነው። በዚያም የቅኔ ትምህርታቸውን በአግባቡ ከተወጡ በኋላ አቋቋም ለመማር አለፉ ማለት ነው። አቋቋም የመጨረሻው የትምህርቱ እርከን ሲሆን፣ ይህንን ያጠናቀቀ የአብነት ተማሪም ከእሱ የሚጠበቀው ሥራ መፈለግ በመሆኑ መምህርም ሥራን ማፈላለግ ያዙ እንደ አጋጣሚ ሆኖ ግን መምህራቸው ለሥራ ተፈልገው አዲስ አበባ ከተማ ባዕታ ለማርያም ገዳም እንዲመጡ ሆነ። በዚህ ወቅት ብቻቸውን መምጣት ያልፈለጉት መምህራቸው ይልቁንም ጎበዝ ጎበዝ ተማሪዎችን መርጠው ወደ አዲስ አበባ ገቡ።

«.....በወቅቱ በጣም ልጅ ነበርኩ፤ ነገር ግን ከመምህሬ ጋር ተመርጬ መምጣቴ ደግሞ በጣም አስደስቶኝ ነበር፤ መምህራችን ሥራቸው በዓታ ለማርያም ቢሆንም እኛ አብረናቸው የመጣነው ደግሞ ግማሾቻችን እዚያው ባዕታ ቤተ ክርስቲያን የቀረነው ደግሞ ኮልፌ ጳውሎስ ቤተክርስቲያን እንድሄድ ሆነ፤ » ይላሉ።

ከነ ደበሷቸው አዲስ አበባን የተቀላቀሉት መምህር ዮሐንስ ሺበሺ ኮልፌ ጳውሎስ ቤተክርስቲያንም በጥሩ ሁኔታ ተቀበላቸው። እሳቸውና ጓደኞቻቸውም የተማሩትን ቅኔ ሲዘርፉ ቃለ እግዚአብሔርን ሲናገሩ ሲቀድሱ፤ ሲዘምሩ ልዩ ስለነበሩ የከተሜው ሰው እጅግ ይደሰትባቸው ነበር። በተለይም የወቅቱ ባለሀብቶች ባለሥልጣናትና መሳፍንቶች በጣም ስለሚደሰቱና ስለሚገረሙባቸው ቤታቸው ድረስ በመሄድ ይጋብዟቸውና ልብስ ይገዙላቸው።

«በወቅቱ ለከተማው ሰው የሚገርም አለባበስ ነበር የምናዘወትረው። የቤተክርስቲያን ሕግና ሥርዓቱን ተከትለን ስለምንለብስ ሰዎች በፍጹም ደስታና ፍቅር እንዲሁም አክብሮት ነበር የሚያዩን በተለይም ባለሥልጣናቱና መሳፍንቱ በዚያ በልጅነት ዕድሜያችን ቅኔ ስንቀኝ ሲያዩን በጣም ይገረሙ ነበር፤ አቋቋም ላይም ሲያዩን የተለየ ስሜት ይፈጥርባቸዋል፤ በዚህም አንዳንዶቹ ልብስ ገንዘብ ይሰጡናል ቤታቸው ወስደው ይጋብዙን ሁሉ ነበር» በማለት ይገልጻሉ።

መምህር በወቅቱ ከተሜው ያሳያቸውን ፍቅር በተለይም የኮልፌ ምዕመናን የነበራቸውን ነገር እስከ ዛሬ ድረስ እንደማይረሱት ይናገራሉ። በዚህም የተነሳ እስከ አሁን ድረስም መኖሪያቸው እዚያው ነው።

### ዘመናዊ ትምህርት ቤት

መምህር ዮሐንስ በአብነት ትምህርቱ ብዙ ርቀት የተጓዙ በርካታ እውቀቶችንም የያዙ ቢሆንም ዘመናዊው ትምህርት ደግሞ ስላስፈለጋቸው ትምህርትን ለመከታተል ቢፈልጉም በተለይም መምህራኖቻቸው የቤተክርስቲያን ሊቃውንቱ ግን እዚያው ቤተክርስቲያን ላይ ቆይተው የእነሱን ወንበር እንዲቀበሉ ፈለጋቸውን እንዲከተሉ ምኞታቸው ስለነበር ወደዘመናዊ ትምህርቱ መግባት ትንሽ አስቸግሯቸው እንደነበር በአንደበታቸው ይናገራሉ።

ያም ቢሆን ግን መድኃኔዓለም አካባቢ «እድገት በጥበብ» የሚባል ትምህርት ቤት ዘመናዊ ትምህርትን ከአራተኛ ክፍል ጀመሩ፤ ነገር ግን ትምህርት ቤቱ የክፍያ ስለነበር እሳቸውም ለመክፈል አቅም ስላነሳቸው ወደመንግሥት ትምህርት ቤት ተዘዋወሩ።

«....በወቅቱ እኔን ጨምሮ ጓደኞቼ በጣም ጎበዝ ነበርን ምናልባት እንግሊዝኛው ትንሽ ያስቸግረን ይሆናል እንጂ በሌላው የሚደርስብን አልነበረም፤ እኔ ስገባ አራተኛ ክፍል ገባሁ በግማሽ ሴሚስተር አምስተኛ ክፍል ገባሁ፤ አምስተኛንም ብዙ ሳልማር ስድስተኛ ገባሁ ፤» በማለት የዘመናዊ ትምህርት ሕይወታቸውን ይናገራሉ፡፡

በወቅቱ «እኛስ ከከተማ ልጆች በምን እናንሳለን የሚል መንፈሳዊ ቅናት በውስጣችን ነበር፤ በተለይም እዚያው ቤተክህነቱ አካባቢ ሆነው ዘመናዊ ትምህርት ተምረው እንግሊዝኛ የሚናገሩ ብሎም 12ተኛ የደረሱ ከዚያም አልፈው ዩኒቨርሲቲ የሚማሩ ልጆች በጣም ያስቀኑን ነበርና እኛም እነሱ የደረሱበት መድረስ ይገባናል ብለን በጣም እንተጋ ነበር፡፡ ለእኛ ያስቸግረን የነበረው ሂሳብ ትምህርት ብቻ ነበ » በማለት ሁኔታውን ያስታውሳሉ፡፡

በአንድ አመት ሦስት የክፍል ደረጃዎችን የተማሩት መምህር ዮሐንስ ስድስተኛ ክፍል ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ባሉበት ወቅት ደብል ቢመቱም ሚኒስትሪ መፈተን አለባቸው ተብሎ ስለተወሰነ እሱንም ወስደው በአንድ አመት ውስጥ ስድስተኛና ሰባተኛ ክፍልን ተምረው አጠናቀቁ።

መምህር ዮሐንስ ሙሉ ዓመት የተማሩት ስምንተኛ ክፍል ነው። ከዚያም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለመማር ወደዊንጌት መሄዳቸውንም ያስታውሳሉ።

«.... በእኛ ዘመን ዊንጌት አዳሪ ትምህርት ቤትነቱን ትቶ ወደመንግሥት ገብቶ ነበርና በትምህርት ቤቱ ታሪክ የመጀመሪያዎቹ የድሃ ልጆችም ነበርን፤ ትምህርት ቤቱ በጣም ውብ ውብ ብቻም ሳይሆን የትምህርት አሰጣጡም ደረጃውን የጠበቀ ነበር፤ እኔም ከ9 ክፍል ጀምሮ እስከ 12 ክፍል ያለውን የትምህርት እርከን እዚያው ነበር ተምሬ የ12 ክፍል መልቀቂያ ፈተና የወሰድኩት» በማለት ይገልጻሉ፡፡

መምህር ዮሐንስ ትምህርቱን ቢወዱትም የሂሳብ ትምህርት ግን ይፈተናቸው ነበር፤ እንግሊዝኛ እንደውም የሚወዱት የትምህርት ዓይነትም ሲሆን እስከ ዛሬም ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ልዩ ትኩረትና ፍቅር እንዳላቸው ይናገራሉ። ሂሳብ ትምህርት ግን በጣም ቢያስቸግራቸውም ራሳቸውን እንዳይችሉ የሚያደርግ ችግር ግን አላስከተለባቸውም።


የ12ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ከወሰዱም በኋላ የመጣላቸው ውጤት ለዲፕሎማ የሚያስገባ ስለነበር በቀጥታ ያመሩት ወደ ኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሆነ። ኮተቤ ኮሌጅም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርትን ለማጥናት መማር ቢጀምሩም ከአንድ ወር የትምህርት ቆይታ በኋላ ግን በአንድ ጓደኛቸው ግፊትና ጉትጎታ ምክንያት ወደ ኢትዮጵያ ቋንቋዎች (አማርኛ ) የትምህርት ክፍል መግባታቸውን ይናገራሉ።

«....ኮተቤ ትምህርት ኮሌጅ ተቀብሎ ያስተምረን የነበረው ማደሪያ ሰጥቶ የንጽህና መጠበቂያ ሳሙና ሳይቀር ተሟልቶልን ከሶፍት አቅም እንዳንቸገር ሁሉ ነገር ተሟልቶ ይቀርብልን ነበር። በዚህም ምንም ችግር አልገጠመኝም፤ ሌላው ደግሞ በወቅቱ እሠራበት የነበረው ጴጥሮስ ወ ጳውሎስ ቤተክርስቲያን ደመወዜን ሳያቋርጡ እየከፈሉ በሚመቸኝ ሰዓት ሄጄ እንዳገለግል ሁኔታዎችን እያመቻቹ አስተምረውኛል። በእውነት የእነሱ ውለታ የሚረሳም አይደለም» በማለት ይናገራሉ።

ነገር ግን አማርኛ ትምህርት ክፍል ላይ ከገቡ በኋላ ትምህርቱ እንደ እንግሊዝኛው ፈታ ያለ ባይሆንላቸውም እንዲሁም ብዙ ሥራን ቢፈልግባቸውም ተመርቀው ሲወጡ ግን ጥሩ ውጤትን ይዘው ነበር።

ትምህርታቸውን አጠናቀው ከተመረቁ በኋላ የተማሩትን ያስተምሩ ዘንድ ዕጣ የደረሳቸው ጎንደር ነበር ፤ በወቅቱ መምህር ዮሐንስም ሆኑ ቤተሰቦቻቸው ጎንደር ሄደው ማገልገላቸውን አልፈለጉም። ግራ በተጋቡበት ወቅትም ባሌ ላይ ባዶ ቦታ እንዳለና እዚያ ሄደው መሥራት እንደሚችሉ አወቁ። በዚህ ተስማምተው ወደ ባሌ ሄደው ሥራ ሊጀምሩ ሲነሱ ሌላ ቅያሪን ይሰማሉ። «የእህል ውሃ ነገር» በሰው ውሳኔ አይሆንምና መምህር ዮሐንስ የጎንደሩን ዕጣቸውን በፍቼ ሰላሌ የሚቀይር የጎንደር ልጅ አገኙ። ይህ ለእሳቸውም ሆነ ለቤተሰቦቻቸው እጅግ አስደሳች ነበርና ዓይናቸውን ሳያሹ ከልጁ ጋር ተቀያይረው የሥራ ቦታቸውን ፍቼ አደረጉ ማለት ነው።

«.... በወቅቱ የሰሜን ሸዋ አውራጃው ሰላሌና




**«.....በወቅቱ በጣም ልጅ ነበርኩ፤ ነገር ግን ከመምህሬ ጋር ተመርጬ መምጣቴ ደግሞ በጣም አስደስቶኝ ነበር፤**

መርሐቤቴ ነበር የሚባለው። እኔም አውራጃው ላይ ሄጄ ዕጣ ሳወጣ ፍቼ የሚል ደረሰኝ ። በጣም ደስ የሚለው ነገር ደግሞ ፍቼ ከዚያ ቀደም ከቤተሰብ ጋር ሆኜ ስለሄድኩኝ አውቀው ነበርና ፍቼ ሲደርሰኝ በጣም ነበር የተደሰትኩት፤ መደሰትም ብቻ ሳይሆን የዕድሜዬን አብዛኛውን ዘመን እያስተማርኩ እየኖርኩበትም ነው» በማለት ያስረዳሉ።

ምንም እንኳን ሀገሩን ስለሚያውቁት ፍቼ ላይ መመደባቸው ደስታን ቢፈጥርባቸውም ለመጀመሪያ ጊዜ ከቤተሰቦቻቸው ራቅ ብለው የሄዱባት በተለይም የመጀመሪያዋ ቀን እጅግ አሰቃቂ እንደነበረች ያስታውሳሉ «...እኔ ኮሌጅም ስማር እዚያው እያደርኩ ነው፤ ከዚያ በፊትም ከቤተሰቦቼ ጋር የኖርኩት እናም ተከፍሎ የሚታደርበትን ማደሪያ (ቤርጎ ) ምን እንደሆነ እንዴት እንደሚታደር አላውቅም ነበር፤ ፍቼ የሄድኩ ቀን ግን የግድ ቤርጎ ይዤ ማደር ነበረብኝና በዚህም በጣም ፍርሃት ውስጥ ገባሁ፤ ነገር ግን ማደሬ ግድ ስለነበር እየፈራሁ አደርኩ።

በነጋታው ጠዋት ቤት ያከራያሉ ወደተባሉት ሴት ዘንድ ስሄድ ሴትየዋ ደግሞ ሌላ ችግር ፈጠሩብኝ። «አንተ አሁን ምን ሠርተህ ነው ቤት ኪራይ የምትከፍለው ብለው በጣም ተቆጡ። መምህር ነኝ ብላቸውም አላምን ስላሉ የቅጥር ደብዳቤዬን አሳይቼ ቤታቸውን አከራዩኝ» ይላሉ።

መምህር ዮሐንስ የመጀመሪያ የሥራ ቀናቸውም ሌላ አስቸጋሪ ሁኔታ ገጥሟቸው ነበር፤ የችግሩ ዋና መንስኤ የእሳቸው ልጅነት ሲሆን ወደተቀጠሩበት ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ሲገቡም ዘበኛው አንዴት ዝም ብለህ ትገባለህ በማለት እንደመቷቸው ያስታውሳሉ። ኧረ ተማሪ አይደለሁም መምህር ነኝ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## ባስራዕዩ - በሻካራማው...

ከ6ኛ ገጽ የዞረ

ቢሉም የሚያምናቸው ስላላገኙ እዚያም የቅጥር ደብዳቤያቸውን አሳይተው ተሰሚነት ማግኘታቸውን ነው በትዝታ የዛሬ 40 ዓመት ትውስታቸውን የሚያወሩት።

መምህር ዮሐንስ ከ30 ዓመት በላይ በየዓመቱ ዝውውር ፈልገው አዲስ አበባ እያሉ ቢሞሉት እህል ውሃቸው ፍቼ ላይ ነውና ሊሳካላቸው አልቻለም።

«...... ፍቼ ለመቆየቴ ትልቁ ምክንያት በሥራዬም ሆነ በአካባቢው ደስተኛ መሆኔ ሲሆን ሌላው ደግሞ ውሃ አጣጪዬን ከዚያው አካባቢ አግብቼ ትዳር መመስረቴ ነው። በነገራችን ላይ የሕዝቡ ፍቅር እርቀሽ እንድትሄጂ አያደርግም። በጣም ደግና ሩህሩህ በሆነ ሕዝብ መካከል መቆየቱም በራሱ ሌላ ቦታ እንዳትፈልጊ ያደርጋል» በማለት ይናገራሉ።

ወትሮውንም ቢሆን አዲስ አበባ መግባትን የትምህርት ደረጃቸውን ለማሻሻል ይፈልጉት የነበረው መምህር ዮሐንስ አዲስ አበባ መግባት ባይችሉም ዋል አደር እያለ እየሰፋ በመጣው የትምህርት ዕድል ተጠቅመው እስከ ሁለተኛ ዲግሪ (ማስተርስ) ድረስ ተምረዋል።

መምህርነት በውስጣቸው ያለው መምህር ዮሐንስ ከ30 ዓመት በላይ አስተምረውም ዛሬም አልሰለቹም፤ ማስተማር ደስታዬ መምህትርነትም ሕይወቴ ነው፤ ከማስተማር ተለይቼ ሌላ ሥራ መሥራት አልችልም ይላሉ።

«... እኔ አሁን የጡረታ ጊዜዬ እየደረሰ ነው ፤ ሆኖም ዓይኔ ማየትና ጉልበቴ መራመድ እስኪሳነው ድረስ ኀብጬ ባስተምር ደስታዬን አልችለውም፤ ምክንያቱም እኔ የተፈጠርኩት ትውልድን ላስተምር ነው» ይላሉ።

### መምህርነትና ደራሲነት

መምህር ዮሐንስ የካበተውን የሕይወትና የሥራ ልምዳቸውን የቤተ ክህነትና ዘመናዊ ትምህርት እውቀታቸውን በአንድ አቀናጅተው በርካታ የሀገር ባለውለታዎችን አፍርተዋል። ለሀገር የጠቀሙ፤ በግላቸውም አንቱታን ያተረፉ በተለያዩ ትልልቅ የመንግሥት የሥራ ኃላፊነቶች ላይ ያሉ እንዲሁም በግላቸው በሠሯቸው ሥራዎች ሚሊየነር የሆኑ ትውልዶችን ያፈሩ መምህር ናቸው። ከዚሁ ጎን ለጎንም በርካታ እውቀቶችን የሚያስጨብጡ ሁለት መጽሐፍትን በ 2014 ዓ.ም ለንባብ አበቅተዋል።

«...... ወደ መጽሐፍ መጻፍ የመጣሁት በጣም ዘግይቼ እንደሆነ ይሰማኛል፤ ከ30 ዓመት በላይ በማስተማር ሥራ ውስጥ የቆየ ሰው ለሀገር ወጥ የሆነ ሥራንም ማበርከት ነበረበት፤ ምናልባት አልታየኝ ወይም አልተመቸኝ ይሁን አላውቅም በጣም ዘግይቼ ነው መጽሐፍ የጻፍኩት፤ በዚህም እቆጫለሁ፤ አሁን ቢሆን ግን መጽሐፍ ጽፌ ማለፍ እንዳለብኝ ሲሰማኝ ነው የተወሰኑ መጽሐፍትን ለትውልድ ጥዬ ለማለፍ የተነሳሁት» ይላሉ።

### ከዩኔታ እስከ ዋቄ ፈታ

ይህ የመምህር ዮሐንስ የመጀመሪያ መጽሐፍ ሲሆን በ28 ምዕራፎች ከፋፍለው በረጅም ዓመታት የማስተማርና ከማኅበረሰቡ ጋር አብሮ በፍቅር ተግባብቶ የመኖር ልምዳቸውን አቀናጅተው የማይገናኙ የሚመስሉ ግን ደግሞ ከመሠረታቸው አንድ የሆኑ ድንቅ ኢትዮጵያዊ ባህላዊ እውነቶችን ለማሳየት ሞክረዋል።

አሁን በሀገራችን ከዚህ ቀደም የማናውቃቸው የተለያየ ማንነት ቋንቋ ብሔር ምናምን ይሉት ዓይነት ውስብስብ ነገሮች ተጀምረዋል። እነዚህን ነገሮች ደግሞ ሕዝቡ ያውቀው ዘንድ እንዲሁም እያንዳንዱ ሕዝብ የራሱ ቋንቋ ባህል እምነትና የአኗኗር ዘዬ እንዳለው ተረድቶ ማክበር እንደሚያስፈልግ እኔም አምኛለሁ ይህንን ደግሞ ሌሎች ያምኑበት ዘንድ ከልጅነቴ ጀምሮ የተማርኩትን ሃይማኖታዊ ትምህርት ከዘመናዊው ትምህርት ጋር አቀራርቤ ለምን የሆነ ድልድይ አላኖርም የሚለው ሃሳብ ወደመጽሐፍ ጽሑፉ እንዳስገባቸው ይናገራሉ።



**«...... ፍቼ ለመቆየቴ ትልቁ ምክንያት በሥራዬም ሆነ በአካባቢው ደስተኛ መሆኔ ሲሆን ሌላው ደግሞ ውሃ አጣጪዬን ከዚያው አካባቢ አግብቼ ትዳር መመስረቴ ነው**

በሌላ በኩል ደግሞ አማራና ኦሮሞ ሕዝቦች ያላቸውን የቅርብ ትስስር አጉልቶ ቢወጣ በሕዝቦቹ መካከል የሚያለያይ የሚያቀያይም ነገር የለም፤ አንዳንዶቻችን ሳናውቅና ሳይገባን ቀሪዎቻችን ደግሞ እያወቅንም ወይ በመሳሳት አልያም ለማሳሳት ብለን ያልሆነ ትርጉም የምንሰጥም እየተስተዋልን ነውና እነዚህን ሁለት ትልልቅ የእምነት ጎራዎች መርምሮ አንድነትና ልዩነታቸውን ማሳየት በአቅሜ አስተዋጽኦ ለማበርከት የተሠራ ነው ይላሉ።

ሃይማኖቶቹም ሆኑ ባህሎቹ ከሚያለያዩን ይልቅ የሚያመሳስሏቸው ነገሮች ይበዛሉ የሚሉት መምህር ዮሐንስ እነዚህ ሕዝቦች ደግሞ በፍቅርና በሠላም የኖሩትን በእነዚህ መመሳሰሎቻቸው መሆኑን ተገነዘብኩኝ። በተለይም ግዕዙን ሳነበው ተመሳሳይ ነው በመሆኑም ለምን ከየኔታ እስከ ዋቄ ፈታ የሚለውን አላሳይም በሚል ተነሳሁ ይላሉ።

ሁሉም እንደሚገነዘበው የኔታ በኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች ዘንድ የሚታወቁ የሃይማኖት ምሰሶ ናቸው፤ ዋቄ ፈና እምነት ደግሞ የትልቅና ሰፊ በርካታ ማኅበረሰብ የሚከተለው እምነት ምሰሶም ነው። በመሆኑ እነዚህን ሁለቱን ምሰሶዎች የተጻፉ የታሪክ ድርሳናትን በመያዝ ማቀራረብ ጥቅም እንዳለውም ማሳያ ነው።

መምህር ዮሐንስ እነዚህን ሁለት አንጋፋ ትውፊቶች ካነበቡትና ከኖሩበት እንዲሁም ከሰሟቸው ነገሮች በመነሳት ኪነ ጥበባዊ ለዛን በመጨመር ከጻፉ በኋላም አቅራቢያቸው ላለው የዞኑ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ያቀረቡት ቢሆንም እነሱ ወደ የሰላሌ ዩኒቨርሲቲ በመጻፋቸው የዩኒቨርሲቲው ባለሙያዎችም ሙያዊ አስተያየትን እንደሰጡበት ይናገራሉ።

በዚህም የዩኒቨርሲቲው ባለሙያዎች በተለይም ይዘቱ ከሥነ ጽሑፍ አንጻር እንዲሁም አንድ ልቦለድ ጽሑፍ ሊያሟላቸው ከሚገቡ መስፈርቶች አንጻር ለሁለት ዓመት ያህል ከታየ በኋላ ሊታረሙ የሚገባቸው አስተያየቶች ተሰጥቷቸው እንዲታተም ስለመፈቀዱ ያብራራሉ።

«....በነገራችን ላይ ባለሙያዎቹም ሲያዩት ደንግጠው ነበር ምክንያቱም ሁለቱ ነገሮች ተጻራሪ ስለሚመስሉ ነው፤ግን ደግሞ ሁለቱም የእምነት ጎራ ናቸው ሕዝብ የሚከተላቸው ናቸው በሌላ በኩል ደግሞ የየራሳቸውን መንፈሳዊ እሴትም ይዘው የሚሄዱ ናቸው። በመሆኑም በአስተሳሰቤም ሆነ የተጻፉትን አንዳንድ ነገሮች ሳይ በርካታ የሚያመሳስሏቸው ነገሮች አሉ» በማለት ያስረዳሉ።

መጽሐፉ አልፎ አልፎ ግዕዝ ተጨምሮበታል የሚሉት መምህር ዮሐንስ ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት ደግሞ የኦሮሞ ማኅበረሰበም ግዕዝ የሱም እንደሆነ ለማሳየት በሌላ በኩል ደግሞ ግዕዝ ለየትኛውም እምነት የሥነ ጽሑፍ መሣሪያ ሆኖ ሊያገለግል እንደሚችልና ከቤተከርስቲያን ውጪ ሌላ አገልግሎት የሌለው ለሚመስላቸው አካላት ማሳያ እንደሆነም ያስረዳሉ።

«.....ግዕዝ ለየትኛውም አምነት የሥነ ጽሑፍ መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል፤ ግዕዝ ከቤተክርስቲያን ውጪ ለሌላ አገልግሎት የማይውል የሚመስከላቸው ሰዎችም የተሳሳቱ መሆናቸውን ሊረዱት ይገባል። ግዕዝ ልክ አንደ አማርኛ እንግሊዝኛ ሌላም ቋንቋ ሁሉ ቋንቋ በመሆኑ በአስፈላጊው ቦታ ሁሉ እየገባ ሥርዓትና ሕጉንም ጠብቀን ማንኛውንም ሥነጽሑፍ ልናቀርብበት እንደምንችል ያሳያል፤ በሌላ በኩልም ሁለቱም ሃይማኖት ላይ ያሉ አንባቢያን የእኛ ነው ብለው እንዲያስቡም ትልቅ አቅም ይፈጥራል» ይላሉ።

መጽሐፉ የሁለቱን ሃይማኖቶች ጥምረት ያሳያል። ይህም ማለት ሁለቱም ሃይማኖቶች መነሻቸውም ሆነ መድረሻቸው ፍቅር ነው ሌላ ነገር የለውም፤ በሌላ በኩልም ሁለቱም ሃይማኖት ላይ ያለው ነገር ማኅበራዊ መስተጋብርን ማሳለጥ ነው፤ በዚህም ሙሉ በሙሉ ተመሳሳይ ናቸው ለማለት ቢከብድ እንኳን ልዩነታቸው ግን እኛ እንደምናስበው የተራራቀ አለመሆኑን ለማሳየት ስለመሆኑም አብራርተዋል።

«......ሁለቱም ሕዝቦች አብረው የኖሩ ወደፊትም የሚኖሩ ናቸው። በሠላምና በፍቅርም የተጋመዱ የኅብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፤ በእምነት ምክንያት መለያየት እንዳይኖር ገብቶንም ይሁን ሳይገባን የአንዱን ከፍ የሌላውን ዝቅ አድርገን እንዳናይ ያስችላል። የኔታም እንደ ገጸባህርይ የወሰድኳቸው ችኩል ያለመሆንን አመዛዛኝነትን ለፍርድና ለነቀፋ አለመቸኮልን በደንብ አድርገው የሚያሳዩ በመሆናቸው ነው። በሌላ በኩልም የኔታ የዋቄፈታን ዋቄ ፈታም የየኔታን እምነቶች እንዲያከብሩና እርስ በእርሳቸው እየተመካከሩ ተከታዮቻችውን በዚያ መንገድ እንዲመሩ ማድረግም የልቦለዱ መነሻና መድረሻ ነው» ይላሉ።

ይህ መጽሐፍም በቅርቡ 29 ምዕራፍ ተጨምሮበት በድጋሚ ሊታተም እንደሆነም ከመምህር ዮሐንስ ሰምቻለሁ።

### ስፌ ወስፌ

የመምህር ዮሐንስ ሁለተኛው መጽሐፍ ስፌ ወስፌ ይሰኛል፤ ስፌ ወስፌ ማለት እዚህና እዚያ (ማዶ ለማዶ) ማለት እንደሆነም ይናገራሉ። መጽሐፉ የግጥም መድብል ከመሆኑም በላይ ያልዳሰሳቸው የሕይወትና የኑሮ ሁኔታዎች ስለሌሉም ነው እንዲህ ያለው ርዕስ የተሰጠው።

«......የግጽም መጽሐፉ ከተራው ግለሰብ ጀምሮ እስከ ቤተመንግሥት ድረስ ያሉትን ይነካል ሕፃን አዋቂ ደሃ ሀብታሙ ሁሉም ተካተውበታል፤ ምንልባት ኪናዊ ቃል አጠቃቀሜ በተለይም በሳል አንባቢያንን ምን ያህል እንዳረካቸው ባላውቅም እኔ ግን የተሰማኝንና ማስተላለፍ የምፈልገውን ሁሉ ተናግሬበታለሁ» ይላሉ።

### መልዕክት

«......መጽሐፎቹ ብዙ ያስተምራሉ ብዬ አልኩራራም ነገር ግን ብዙ እውቀው ዝም ላሉ ጸሐፍት ማነቃቂያ እንደሚሆን ግን አምናለሁ። በሌላ በኩል አንጋፋም ይሁን ጀማሪ ጸሐፍት ወደ ጽሑፍ ሥራው ሲገቡ በተቻለ መጠን የሕዝቦችን የቆየ ማንነት የሚያሳይ ለመተሳሰራቸው ምክንያት የሆነውን ነገር አጉልቶ የሚያወጣ እንጂ የሚያቃቅርና የሚያለያይ ጽሑፍ አለመጻፍ ያስፈልጋል። መምህራንም በሙያቸው ላይ ትኩረት አድርገው ለትውልዶች አንድ አንድ ቅርስ አስቀምጠው ለመሄድ ቢያስቡ መልካም ነው» በማለት መልዕክታቸውን ያስተላልፋሉ።

# የዩኔስኮ - የዓለም ቅርስ የመምረጫ መስፈርት

**ዳግም ከበደ**

ቅርሶች ያለፈውን፣ ዛሬ ላይ የምንኖረውን እና ወደፊት የሚከሰተውን ሁነት የሚወክሉ ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉ የሰው ልጅ ሀብት ናቸው። ባህላዊ እና ተፈጥሯዊ ቅርሶቻችን የማይተኩ የሕይወት ምንጮች እና መነሻዎች እንደሆኑ ይታመናል። ከዚህ መነሻ ዩኔስኮ ለሰብአዊነት የላቀ ጠቀሜታ ያላቸውን የባህልና የተፈጥሮ ቅርሶችን የመለየትና የመጠበቅ ሥራን ያበረታታል።

ዓለማችን ላይ እነዚህን መስፈርቶች የሚያሟሉ ሀብቶችን የመመዝገብ እንዲሁም የማስተዋወቅ ድርሻንም ይወስዳል። ሀገራትም ይህንን ዕድል በመጠቀም መስፈርቱን የሚያሟሉ ሀብቶቻቸውን በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) ለማስመዝገብ ይሠራሉ። ይህ ዕድልም ዓለም አቀፍ ቱሪስቶችን ለመሳብ፣ ሀገርን የበለጠ ለማስተዋወቅና ገፅታን ለመገንባት ይጠቀሙበታል።

የማንነት መገለጫ የሆኑ ሀብቶችን ከማስተዋወቅ በዘለለ በቱሪዝም ዘርፉ ሀብቶቹ የኢኮኖሚ የጀርባ አጥንቶች ናቸው። ኢትዮጵያ እነዚህን መሰል ሀብቶች ለቱሪስት መስህብነት እንዲውሉ በመሥራትና ቱሪዝምን ከዋና ዋና ዘርፎች መካከል አንዱ በማድረግ ትታወቃለች። በተፈጥሮ፣ ታሪክ፣ ባህልና አርኪዮሎጂ ዘርፍ የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ 15 የሚደርሱ ቅርሶችን ለዓለም አበርክታለች። ከእነዚህ ውስጥ በ2016 ዓ.ም መባቻ በመስከረም ወር በአዲሱ ዓመት ስጦታነት በይፋ የተመዘገቡ የባሌ ብሔራዊ ፓርክ እና የጌዲዮ ባህላዊ መልከዓ ምድርና ጥብቅ ደን ይገኙበታል።

ባህላዊና ተፈጥሯዊ ሀብቶች በዓለም ቅርስነት ለመመዝገብ በጠንካራ መስፈርቶች ተገምግመው ማለፍ ይኖርባቸዋል። ኢትዮጵያ ያስመዘገበቻቸው፣ በጊዜያዊነት በዩኔስኮ መዝገብ ላይ የሰፈሩ ተጨማሪ ሀብቶችን ለመመዝገብ በሂደት ላይ የሚገኙ ሌሎች መስህቦች እነዚህን ዓለም አቀፍ መስፈርቶች በሙሉ ያሟሉ እንደሆኑ የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ።

ከላይ ያነሳነውን ርዕሰ ጉዳይ በዝርዝር ለማውሳት እንዲያመቸን የዝግጅት ክፍላችን በዚህ ወር በይፋ በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡትን የጌዲዮ መልካምድርና ጥብቅ ደን እንዲሁም የባሌ ተራራዎች በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡበትን መስፈርት ለመዳሰስ ፈቅዷል። ከአፍሪካ የሰው ልጅ ወካይ ቅርሶችን በቀዳሚነት በማስመዝገብ ወደር የማይገኝላት ኢትዮጵያ ሀብቶቹን በዩኔስኮ ለማስመዝገብ ያለፈችባቸው ሂደቶችም ይጠቀሳሉ።

ሀገሪቱ ያሟላቻቸውን መስፈርቶች በተመለከተ በሂደቱ ተሳታፊ የነበሩት ባለሙያ አቶ አንዷለም ግርማይ በኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን ውስጥ በቅርስ ጥናትና ምርምር ለረጅም ጊዜ ሠርተዋል። ሀብቶቹን ለማስመዝገብ በዳይሬክተርነት እየመሩ ሲሠሩ የነበሩና አሁን ደግሞ በብሔራዊ ሙዚየም መሪ ሥራ አስፈፃሚ በመሆን እያገለገሉ ይገኛሉ።

አቶ አንዷለም እንደሚናገሩት፤ የታሪክ፣ የባህል፣ የአርኪዮሎጂና የተፈጥሮ ቅርሶችን በዓለም አቀፍ ቅርስነት ለማስመዝገብ ጠንካራ መስፈርቶችን ማሟላት የግድ ይላል። ዩኔስኮም የሰው ልጅ ወካይ ቅርሶችን ለማስመዝገብ አስር የሚደርሱ መስፈርቶች አሉት። ከእነዚህ ውስጥ በጌዲዮ ዞን የሚገኘው የጌዲዮ ማኅበረሰብ ባህላዊ መልከዓ ምድርንና ጥብቅ ደንን ለመመዝገብ በባህል ዘርፍ ብቻ ከተቀመጡ ስድስት መስፈርቶች በዋናነት ሁለቱን እንዳሟላ አቶ አንዷለም ይናገራሉ። በዩኔስኮ ሀብቱን ለማስመዝገብ ከእነዚህ መስፈርቶች ውስጥ አንዱን ብቻ ማሟላት በቂ እንደሆነም ይገልፃሉ።

መሪ ሥራ አስፈጻሚው እንዳመለከቱት፤ የጌዲዮ ባህላዊ መልከዓ ምድርና ጥብቅ ደን ለዓለም ቅርስ በዕጩነት የቀረበበት መምረጫ መስፈርትን ሲያብራሩ በስድስት መመዘኛዎች ውስጥ እንደተገመገመ ይናገራሉ። ዩኔስኮ ባህላዊ ሥርዓቱን እና በባህላዊ መንገድ የሚጠበቁ ተፈጥሮዎች እንዲሁም እሴቶችን ለመመዝገብ ከሚጠቀማቸው መመዘኛዎች ውስጥ አንዱ መስህቡ «ድንቅ የሰው ልጅ የፈጠራ ክህሎትን የሚወክል» መሆኑን ማረጋገጥ እንደሆነ ይናገራሉ። በሁለተኝነት ደግሞ መሠረታዊ የሆኑና «በጊዜ ሂደት የሚፈጠሩ የሰው ልጅ እሴቶችን የሚወክሉ» የለውጥ ሂደቶችን ወይም «የዓለም የባህላዊ ሁኔታዎችን የሥነ ሕንፃ ወይም የቴክኖሎጂ እድገቶች፣ የሐውልት ጥበቦችን፣ የከተማ ፕላኖችን ወይም መልከዓ ምድር የሚወክል» መሆን እንደሚጠበቅበት ይገልፃሉ። የጌዲዮ ባህላዊ መልከዓ ምድርም ዩኔስኮ በሁለተኛነት ያስቀመጠውን ይህንን መስፈርት ሙሉ ለሙሉ እንዳሟላ ይናገራሉ።

> በመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎቹ በዩኔስኮ ድረ ገጽ እና በመሳሰሉት የማሰራጫ ዘዴዎች የሚለቀቁ መሆኑ ቅርሶቹ በሀገር አቀፍ ደረጃ አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና እንዲያገኝ ያደርገዋል። በሌላ መልኩ የቱሪስት መስህብነታቸው እንዲጨምር፤ በዚያው ልክ ከዘርፉ የሚገኘው የውጭ ምንዛሪ እንዲያድግ አስተዋፅኦ ያደርጋል

ሦስተኛውና ባህላዊ ቅርሶች የሚመዘገቡበት የዩኔስኮ መስፈርት «ህያው የሆነ ወይም በአንድ ወቅት የተከሰተ ወይም ተከስቶ የጠፋ ድንቅ ባህል ወይም ሥልጣኔ የሚዘክር» መሆኑ ነው የሚሉት መሪ ሥራ አስፈፃሚው አቶ አንዷለም፣ በዓለማችን ላይ ያሉ ሀብቶች በቅርስነት ለመመዝገብ ይህንን ማሟላት እንደሚጠበቅባቸው ይናገራሉ። የጌዲዮን ጨምሮ በኢትዮጵያ ውስጥ በባህል ዘርፍ በቅርስነት የተመዘገቡ ሀብቶችም ይህንን መስፈርት እንዳሟሉ ይገልፃሉ።

«የጌዲዮ ባህላዊ መልከዓ ምድር በቀዳሚነት ካሟላቸው መስፈርቶች መካከል ዩኔስኮ ያስቀመጠው አራተኛው መመዘኛ አንዱ ነው» የሚሉት አቶ አንዷለም፤ ይህም መስፈርት ቅርሱ በዓይነቱ ልዩ የሆነ የግንባታ፣ የሥነ ሕንፃ ወይም የቴክኖሎጂ የፈጠራ ውጤት በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ያለፈውን ውጣ ውረድ የሚያሳይ መልክዓ ምድር መሆን እንደሚጠበቅበት የሚገልፅ መሆኑን ይናገራሉ። ከዚህ አንፃር ጌዲዮም በሜጋሊቲክ ሐውልቶቹ በመልካ ምድሩና ባህላዊ የተፈጥሮ አጠባበቅ ሥርዓቱ መስፈርቱን ሊያሟላ እንደቻለ ይገልፃሉ።

ሌላኛውና አምስተኛው የዩኔስኮ መስፈርት ቅርሶች «ባህላዊ የሰው አሰፋፈርን፣ የመሬት አጠቃቀምን፣ ወካይ ባህልንና ሰው ከአካባቢው ጋር ያለውን ግንኙነት በተለይም ሊቀለበስ የማይችልን ለውጥ በማሳየት ረገድ በምሳሌነት ሊገለጹ የሚችሉ ቦታዎች» መሆናቸውን የሚገልፁ እንደሆኑ መረጋገጥ እንዳለባቸው የሚናገሩት አቶ አንዷለም፤ በተጨማሪም በስድስተኛ መስፈርትነት ቅርሶች «የተለዩ ወይም ዓለም አቀፍ ጠቀሜታ ያላቸው በቀጥታና ተጨባጭ በሆነ መንገድ ከድርጊቶች፣ ህያውነት ካላቸው ወግና ልማዶች፣ አስተሳሰቦች፣ እምነቶች የሥነ ጥበብና የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ጋር ተያያዥነት ያላቸው እንዲሆኑ እንደሚጠበቅ በሕግና ደንቡ መዘርዘሩን ይናገራሉ። ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያ ያስመዘገበቻቸው ቅርሶች እነዚህን መመዘኛዎች እንደሚያሟሉ ይናገራሉ።

የኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን የሕዝብና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ዳይሬክተር ወይዘሮ ነጃት ጀማል ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፤ ኢትዮጵያ የበርካታ ብሔረሰቦች ሀገር በመሆኗ ብዛት ያላቸው ባህላዊና ተፈጥሯዊ ቅርሶች ባለቤት ነች። በዚህ ምክንያት ለቅርሶች ጥበቃ እየተሰጠ ያለው ትኩረት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ሊሄድ መቻሉን ይገልፃሉ።

ዳይሬክተሯ እንደሚገልፁት፤ ኢትዮጵያ በሀገሪቱ የሚገኙ የመስህብ ሀብቶች ሁሉንም መመዘኛዎች አሟልተው በዓለም ቅርስነት እንዲመዘገቡ፣ እንዲጠበቁ፣ ለማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች እንዲውሉና ማኅበረሰቡን እንዲወክሉ ለማስቻል የተለያዩ የሕግ ሥርዓትና ማዕቀፎች ተዘጋጅተው ተግባራዊ እየሆኑ ይገኛሉ። ከዚህ ውስጥ የሚከተሉት ስምምነቶችና የሕግ ማዕቀፎች ይገኙበታል።

ከእነዚህ እርምጃዎች መካከል እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1972 የባህልና የተፈጥሮ ቅርሶች ጥበቃ ስምምነት መሠረት ሀገራት በዩኔስኮ የባህል፣ የተፈጥሮ እና የሁለቱ ጥምር መስፈርቶችን የሚያሟሉ ቅርሶችን በዓለም አቀፍ ቅርስ ዝርዝር ውስጥ የማስመዝገብ ሥርዓት መሆኑን ወይዘሮ ነጃት ይገልፃሉ። በተመሳሳይ በ1987 የፀደቀው የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ባህላዊ እሴቶቻቸውን በነፃነትና በእኩልነት የመግለጽ፣ የማሳደግና የመንከባከብ መብት መደንገጉን አውስተዋል።

የባህል ፖሊሲን በሚመለከት ተመሳሳይ እርምጃ መኖሩን የሚገልፁት ዳይሬክተሯ፤ በ1990 ዓ.ም የወጣው የባህል ፖሊሲ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ባህላዊ እሴቶች እንዲመዘገቡ፣ እንዲጠኑ፣ እንዲጠበቁና በእኩልነት እንዲታወቁ እንዲሁም ለማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት እንዲውሉ አቅጣጫ ማመለከቱን በምሳሌነት ይጠቅሳሉ። ይህም መስህቦቹን በዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብና የተጠቀሱትን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ እንደሆነም ይገልፃሉ።

ዳይሬክተሯ እንደሚያስረዱት፤ ከላይ ከተነሱት ማዕቀፎች ባሻገር በ1992 ዓ.ም የወጣው የቅርስ ጥናትና አጠባበቅ አዋጅ ባህላዊ ቅርሶች ተመዝግበው፣ ተጠንተው፣ ተጠብቀውና ተዋውቀው ለዘለቄታዊ ልማት እንዲውሉና ባህላዊ ይዘታቸውን ጠብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉበትን መንገድ መደንገጉን አንስተው፣ በዚህ ሕግና ድንጋጌ መሠረት እየተሠራ እንደሆነ ይናገራሉ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የቅርሱን ጥበቃ ለማገዝ የወጡ ሌሎች የሕግ ማዕቀፎች መኖራቸውንም ገልፀውልናል።

ወይዘሮ ነጃት በቅርቡ በዓለም ቅርስነት በዩኔስኮ እውቅና አግኝተው የተመዘገቡት የጌዲዮ ባህላዊ መልከዓ ምድርና ጥብቅ ደን እንዲሁም የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክ እውቅና ማግኘታቸው በርካታ ፋይዳዎችን ለኢትዮጵያ እንደሚያስገኙ ይጠቁማሉ።

በተለይ የዩኔስኮን መስፈርት ማሟላታቸውና መመዝገባቸው በርካታ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አላቸው የሚሉት ዳይሬክተሯ፤ በመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎቹ በዩኔስኮ ድረ ገጽ እና በመሳሰሉት የማሰራጫ ዘዴዎች የሚለቀቁ መሆኑ ቅርሱ ከሀገር አቀፍ ደረጃ አልፎ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና እንዲያገኝ ያደርገዋል ይላሉ። በሌላ መልኩ የቱሪስት መስህብነታቸው እንዲጨምር፤ በዚያው ልክ ከዘርፉ የሚገኘው የውጭ ምንዛሬ እንዲያድግ አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ያስረዳሉ።

«ለቅርሶቹ መንግሥታዊ አካላትና ሌሎች ተቋማት ትኩረት የሚሰጡት በመሆኑ ቅርሶቹ ከቀድሞ በተሻለ ሁኔታ እንክብካቤና ጥበቃ ይደረግላቸዋል» የሚሉት ዳይሬክተሯ፣ ይህም ቅርሶቹ ይዘታቸውን ጠብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፉ እንደሚረዳ ይናገራሉ። በሌላ በኩል ቅርሶቹ በዓለም አቀፍ ጥበቃና እንክብካቤ የሚያገኙበት መንገድ እንደሚመቻችላቸው ያስረዳሉ።

እንደ ዳይሬክተሯ ገለፃ፤ የዩኔስኮን መስፈርት አሟልተው የተመዘገቡት እነዚህ ቅርሶች የሀገር ውስጥ ቱሪስትን በማበረታታት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እርስበርስ ተዋውቀውና ተከባብረው በሰላም አብረው የሚኖሩበትን ሥርዓት አጠናክሮ ለመቀጠል እንደሚረዱ ይናገራሉ። በተጨማሪም በዓለም አቀፍ ደረጃ ቅርሶቹ እውቅና ማግኘታቸው ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች አጥኚዎችንና ተመራማሪዎችን በመሳብ ተጨማሪ ውጤቶች እንዲገኙ በር ከፋች መሆኑን ያስረዳሉ።

### እንደ መውጫ

የኢትዮጵያን ባህላዊ፣ ተፈጥሯዊና አርኪዮሎጂካል ሀብቶች በዓለም ቅርስነት ማስመዝገብ ተገቢ ቢሆንም የመጨረሻው ግብ እርሱ ብቻ መሆን የለበትም። ይህንን ጉዳይ በዘርፉ በርካታ ዓመታት የሠሩ ምሁራንም ይስማሙበታል። በተለይ የዓለም ቅርስነት መመዘኛን የሚያሟሉ (ለምሳሌ በቅርቡ እንደተመዘገቡት የጌዲዮና የባሌ የመሰሉ) ሀብቶች ዓለም አቀፍ እውቅና እንዲያገኙ ከመሥራት በተጓዳኝ ቅርሶቹ ተጠብቀው፣ ለምተውና ተዋውቀው፣ ይዘታቸውን ጠብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፉ በተለያዩ እርከኖች ላይ የሚገኙ የማኅበረሰብ አካላት ተሳትፎ በማድረግ መጠበቅና ማልማት እንዲችሉ ማስገንዘብ እንደሚገባ ያሳስባሉ። በተጨማሪም ወጣቶች ስለቅርሶቹ ምንነት፣ ይዘታቸውና ታሪካቸው ለማኅበረሰቡ የሚሰጠውን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ በተመለከተ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጠንቅቀው መማር፣ ማወቅ፣ መከታተልና መተግበር እንደሚኖርባቸው ምክረ ሃሳብ ሲሰጡ ይደመጣል።

በልዩ ልዩ መድረኮች ላይ ሲነገሩ ከሚደመጡ ምክረ ሃሳቦች መካከል በዚህ ላይ የመገናኛ ብዙኃን የሚኖራቸው ጉልህ ፋይዳ ነው። በዋናነትም በተለያዩ መገናኛ ብዙኃንም ኅብረተሰቡን ባሳተፈ መልኩ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት ከቅርሶቹ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጠቃሚ መረጃዎች ዕውቀትና ክህሎትን ወደ ተተኪው ትውልድ ማስረጽ እንደሚያስፈልግ ሲነገር ይደመጣል። መንግሥትም ከቅርሶቹ ጋር በተያያዘ ሕጋዊ ማዕቀፎችን ከማውጣት በተጓዳኝ በጀት በመመደብና የቅርሱ ማከናወኛ ሥፍራዎችን የመጠበቅና መሠረተ ልማት በመገንባት እንዲሁም የማልማት ሥራውን አጠናክሮ መቀጠል እንደሚኖርበት ከሚሰጡት ምክረ ሃሳቦች መካከል ይጠቀሳል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## የሳምንቱ ቅይጥ ታሪኮች

**ዋለልኝ አየለ**

ዓመተ ምህረት ከቀየርን እነሆ ሁለት ሳምንታት አለፉን። በታሪክ ውስጥ ዓመተ ምህረት ትልቅ ቦታ አለው። በምንጠቅሳቸው ታሪኮች ውስጥ ‹‹ከ... ዓመታት በፊት›› የምንለው ቁጥሩ እየጨመረ ይሄዳል ማለት ነው። በሌላ በኩል አዳዲስ ተጨማሪ ታሪኮች ይኖራሉ ማለት ነው። ለምሳሌ፤ ከዚህ በፊት በዚህ ሳምንት የሙዚቃው ንጉሥ ጥላሁን ገሠሠ ይታሰብ ነበር። እነሆ ከዚህ ዓመት በኋላ ደግሞ አርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅ ተጨመረ ማለት ነው። አንደኛው በውልደት አንደኛው በሞት የዚህ ሳምንት ክስተቶች ይሆናሉ ማለት ነው። ‹‹ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም›› የሚባለው ለታሪክ ክስተቶች ነው።

ከዘመናት በፊት የተከሰቱ የዚህ ሳምንት የታሪክ ክስተቶችን ስናስታውስ ቅይጥ ሆነው እናገኛቸዋለን። ለዛሬው አንዱን ብቻ መርጠን በዝርዝር ከማየት ይልቅ የሁሉንም አጠር አጠር አድርገን ማየት መረጥን። በቀናቸው ቅደም ተከተል መሠረት እንያቸው።

ከ77 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መስከረም 15 ቀን 1939 ዓ.ም የመጀመሪያው የአማርኛ ረጅም ልብወለድ መጽሐፍ (‹‹ጦቢያ››) ደራሲ ፕሮፌሰር አፈወርቅ ገብረኢየሱስ ዘብሄረ ዘጌ አረፉ። አፈወርቅ ገብረኢየሱስ በሀገርኛ ቋንቋ በመጻፍ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የመጀመሪያው ጥቁር አፍሪካዊ የተባሉ ናቸው። በፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ ወቅት ‹‹የኢጣሊያ መንግሥት መልዕክተኛ ሆነው አገልግለዋል›› ተብለው የዕድሜ ልክ እስራት የተፈረደባቸው፣ የእቴጌ ጣይቱ ዘመድ (ግን ደግሞ እቴጌዋ በአንድ የሥዕል ሥራ ምክንያት የጠሏቸው) ናቸው። አፈወርቅ ገብረኢየሱስ የኢጣሊያ መንግሥት መልዕክተኛ ሆነው በማገልገላቸው ከመታሠራቸውም ባሻገር በታሪካቸው ‹‹ባንዳ›› የሚል ወቀሳ አትርፈዋል።

‹‹ጦቢያ›› በሚለው መጽሐፋቸው የመጀመሪያው ረጅም ልቦለድ ጸሐፊ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። መጽሐፉ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ‹‹አጤ ምኒልክ›› የሚለውን በመጨመር ሁለት መጽሐፍ አንድ ሆኖ (በማዟዟር) በገበያ ላይ ይገኛል። በብዙ የሥነ ጽሑፍ መድረኮችና ውይይቶችም ‹‹ጦቢያ›› የሥነ ጽሑፍ መነሻ ተደርጋ ትጠቀሳለች።

አሁን ደግሞ 357 ዓመታትን ወደኋላ እንሂድ። በዚሁ ሳምንት መስከረም 15 ቀን 1659 ዓ.ም ከጎንደር ነገሥታት አንዱ የነበሩት አፄ ፋሲል አረፉ። የአጼ ፋሲል ታሪክ ከጎንደር ነገሥታት ሁሉ ጎላ ብሎ ይታወቃል። አጼ ፋሲል ከ18 የጐንደር ነገሥታት አንዱ ሲሆኑ የአጼ ሱስንዮስ ልጅ እና የአጼ ዮሐንስ አዕላፍ ሰገድ አባት ናቸው። አጼ ፋሲል በታሪክ ውስጥ ዛሬ ድረስ ሕያው እንዲሆኑ ካደረጓቸው ነገሮች አንዱ የዓለም ቅርስ የሆነው የፋሲል ግንብ ነው። አጼ ፋሲል ፋሲለደስ እየተባሉም ይጠራሉ። በዚህም ምክንያት በስማቸው ትምህርት ቤቶች እና ክፍለ ከተሞች ተሰይመዋል።

ከ94 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት በደመራ ዕለት መስከረም 16 ቀን 1922 ዓ.ም ‹‹ሞገደኛው›› ደራሲና ጋዜጠኛ መንግሥቱ ገዳሙ ተወለደ። መንግሥቱ ገዳሙ በርካታ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች አሉት። መንግሥቱ ‹‹ሞገደኛው›› የሚለው ሥያሜ የተሰጠው ከልጅነቱ ጀምሮ ችኩል፣ ቁጡና ስህተቶችን የማይታገስ ስለነበር ነው ይባላል። በዚህም ምክንያት ሞገደኛ የሚል ቅጽል ስም ተሰጥቶት ያ ስም አብሮት ዘለቀ። ካደገ በኋላም የሰውየው ባህሪ ወጣ ያለ የሚባል ነበር። በሕይወት እያለ ‹‹መንግሥቱ ገዳሙ ሞቷል›› ብሎ በራሱ ላይ መርዶ ያስነገረ ደፋር ነው። በተደጋጋሚ ሚስት እያገባ በመፍታት ‹‹የሴቶችን ባህሪ ለማወቅ ነው›› በማለት በራሱ ሕይወት ላይ ጥናት ያደርግ ነበር። የሚሠራበት መሥሪያ ቤት ውስጥ በርኖስ ለብሶ በመግባት ‹‹ኧረ ባክህ የሥራ አለባበስ ሥነ ሥርዓት አይደለም›› ሲሉት ‹‹ባህሌን ለማስተዋወቅ ነው›› በማለት ይሟገት ነበር። በአጠቃላይ በእነዚህ ባህሪያቱ ‹‹ሞገደኛው›› የሚል ቅጽል ስም አትርፏል።

ከ107 ዓመታት በፊት የመስቀል ዕለት መስከረም 17 ቀን 1909 ዓ.ም ልጅ ኢያሱ ከሥልጣን ተሽረው፣ ዘውዲቱ ምኒልክ ‹‹ንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ›› ተብለው በአባታቸው፣ በዳግማዊ ምኒልክ፣ ዙፋን ተቀመጡ። ደጃዝማች ተፈሪ መኮንንም ‹‹ራስ ተፈሪ›› ተብለው አልጋ ወራሽ ሆኑ። ሙሉ ዝርዝሩን በጥቅምት ወር የሰገሌ ጦርነትን በምናስታውስበት ታሪክ እናስነብባችኋለን።

ከ83 ዓመታት በፊት ልክ የመስቀል ዕለት መስከረም 17 ቀን 1933 ዓ.ም ዝነኛው ድምጻዊ ጥላሁን ገሰሰ ተወለደ። ታሪክህ ከበዓል አይራቅ የተባለው ጥላሁን ገሠሠ የመስቀል ዕለት ተወልዶ ከ68 ዓመታት በኋላ በፋሲካ በዓል ዕለት አረፈ። ፋሲካ የሚውልበት ቀን ስለሚለያይ በየዓመቱ የፋሲካ ዕለት ላይታወስ ይችላል። ሆኖም ግን ያረፈበት ሚያዝያ 11 ቀን 2001 ዓ.ም ይታወሳል። ጥላሁን ገሠሠ በዚህ ዓመት በብዙ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ሲታወስ አስተውያለሁ።

መስከረም 17 ቀን በዓመቱ ጥላሁን ገሠሠን እያስታውስን ሳለ፤ አርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅም በዚህ ዓመት የዚሁ ታሪክ አካል ሆነ። አርቲስት ማዲንጎ አፈወርቅ በድንገት ሕይወቱ ያለፈው ከአንድ ዓመት በፊት መስከረም 17 ቀን 2015 ዓ.ም ነበር።

ከ63 ዓመታት በፊት መስከረም 17 ቀን 1953 ዓ.ም ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረችበት ወቅት በልዩ ልዩ መንገዶች ለኢትዮጵያ አጋርነታቸውን ያሳዩት እንግሊዛዊቷ የኢትዮጵያ ጠበቃና ባለውለታ ወይዘሮ ሲልቪያ ፓንክረስት አረፉ። ሲልቪያ ፓንክረስት የታዋቂው የታሪክ ምሁርና ልክ እንደርሳቸው ሁሉ የኢትዮጵያ ባለውለታ የነበሩት የፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት እናት ናቸው።

ከ159 ዓመታት በፊት መስከረም 19 ቀን 1857 ዓ.ም በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ቁንጅና ውድድር ተካሄደ። ብዙም ሲነገርለት ስለማይሰማ፤ የጳውሎስ ኞኞን አጤ ቴዎድሮስ መጽሐፍ ዋቢ በማድረግ ዘርዘር አድርገን እንየው።

የመስቀል በዓል በዋለ በሁለተኛው ቀን፣ ከልደታ ምሥራቅ ለአበራ ጊዮርጊስ ሰሜን ከሆነችው በቀሃ ወንዝ አጠገብ፣ አጤ ሰቀላ ላይ ከምትገኘው ኮረብታ ላይ የንጉሠ ነገሥቱ ሸራ ድንኳን ተተከለ። ከጧቱ ሦስት ሰዓት ጀምሮ የከተማውና የገጠሩ ሕዝብ በዓሉ ወደሚከበርበት ሜዳ ይጎርፍ ጀመር።

ከረፋዱ አራት ሰዓት ሲሆን ምርጥ መሣሪያ የያዙ ወታደሮችና አጋፋሪዎች ሰልፈኛውን ለማስተናበርና ፀጥታውን ለማስከበር በበዓሉ ሜዳ ተሰማሩ። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ፊታውራሪ ገብርዬ በሠራዊታቸው ታጅበው ሰንደቅ ዓላማ እያውለበለቡ አጤ ሰቀላ ደረሱና የዙፋኑን አቀማመጥ ተመለከቱ።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ ንጉሠ ነገሥቱ ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ በፈረሶች በሚሳብ ሰረገላ ላይ ተቀምጠው ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ቤል ባሰለጠናቸው ወታደሮች ታጅበው መጥተው በዙፋናቸው ላይ እንደተቀመጡ እምቢልታና መለከቱ ተብላላ፤ አጅብር አጅብር፣ ውጋው ውጋው እያለ ነጋሪት ይጎሰም ጀመር።

ዘፋኞች ይዘፍናሉ፤ አዝማሪዎች ይዘምራሉ፤ ወታደሮች ይጨፍራሉ። በዚህ ዓይነት ይዞታ ተድላና ደስታ ሆኖ ሲደባለቅ በመካከሉ ለውድድሩ የታጩት ወይዛዝርት ጥልፍ ቀሚሳቸውን እያንሰረተቱ፣ ተቀብተውና ተኳኩለው ወደተዘጋጀላቸው ቦታ ያልፋሉ።

ቀጥሎም ምርጫው በሚፈፀምበት ጎል እየገቡ ውበታቸውና ደም ግባታቸው፣ የላሕየ ገፃቸው አወራረድ፣ የፀጉራቸው ስሬት፣ የቁንዳላቸው ርዝመት፣ ሽንጣቸው፣ ዳሌያቸውና ተረከዛቸው እየተመረመረ የምርጫው ሥነ ሥርዓት ይጀመራል። እንዲህ እየተደረገም ከሰቀልት ወረዳ ከመቋሚያ ማርያም የመጣችው ትውልዷ ከመቄት አዝማቾች ወገን የሆነችው የደጃዝማች ይልማ አሰፋ ልጅ፣ ጣይቱ ይልማ አንደኛ ስትሆን፣ ከጎንደር አዲስ ዓለም የመጣችው የመሐመድ ኩርማን ሚስት የሼህ መሐመድ ጌታ ልጅ፣ ተዋበች መሐመድ ደግሞ በፀጉሯ ማማር፣ በቁንዳላዋ አወራረድና መርዘም ሁለተኛ ደረጃን አገኘች።

ከዚህ በኋላ ፊታውራሪ ገብርዬና ሊቀ መኳስ ዮሐንስ ቤል የምርጫውን ውጤት ለንጉሠ ነገሥቱ ለመንገር ወደ ዙፋኑ ቀረቡ። ወዲያውም ጣይቱ ይልማ አንደኛ፣ እንዲሁም ተዋበች መሐመድ ጌታ ሁለተኛ መሆናቸውን ከገለፁ በኋላ ተመራጮቹ ከዙፋኑ ፊት በመቅረብ እጅ እየነሱ ሽልማታቸውን ተቀብለው የበዓሉ ፍፃሜ ሆነና እንደተለመደው በሰባት ሰዓት ለመሳፍንት፣ ለሊቃውንት ለመኳንንትና ለካህናት የምሳ ግብዣ ተደረገ።

ከውድድሩ በኋላ አርማኤል (ወርመር) የተባለው በጋፋት የመድፍ ሠራተኞች አለቃ አንደኛ የወጣችውን ጣይቱ ይልማን በሚስትነት አግብቶ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወልደዋል። ጋይንት ውስጥ አሁንም በአርማኤል ስም የሚጠራ መሬት አለ።

በምዕራቡ ዓለም ደግሞ ዘመናዊ የቁንጅና ውድድር መካሄድ የጀመረው በ1831 ዓ.ም በስኮትላንድ እንደሆነ የታሪክ ማስረጃዎች ያሳያሉ። በወቅቱ ተደርጎ በነበረው ውድድር ያሸነፈችው ከገዢ መደብ አባላት የሆነች ሴት እንደነበረች ተፅፏል።

በ1847 ዓ.ም በአሜሪካ የቁንጅና ውድድር ለማድረግ ተሞክሮ ብዙ ሳይጓዝ መቋረጡም ይነገራል። የቁንጅና ውድድር በመላው ዓለም በስፋት እየታወቀ የመጣው ግን በ1881 ዓ.ም በቤልጂየም ከተካሄደው የቁንጅና ውድድር ወዲህ እንደሆነ ማስረጃዎቹ ያመለክታሉ። ለማንኛውም ኢትዮጵያ የቁንጅና ውድድርን የጀመረችው ከ159 ዓመታት በፊት ነው።

ከ88 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መስከረም 23 ቀን 1928 ዓ.ም ፋሲስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን ወረረች። ይህም የአምስት ዓመቱ የፋሽስት ጣሊያን ቆይታ መጀመሪያ ሆነ ማለት ነው።

ከ107 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መስከረም 24 ቀን 1909 ዓ.ም ንጉሥ ሚካኤል አሊ በልጃቸው፣ ልጅ ኢያሱ ከሥልጣን መወገድ ምክንያት ተበሳጭተው ጦራቸውን አስከትተው ወደ ሸዋ እየገሰገሱ እንደሆነ የሰሙት የማዕከላዊው መንግሥት ሹማምንት (የሸዋ መኳንንት) ለንጉሥ ሚካኤል ደብዳቤ ጻፉላቸው። ደብዳቤውም ይህ ነበር።

‹‹...ይድረስ ከንጉሥ ሚካኤል። ዘስልጣኑ ጽሑፍ ዲበ መትከፍቱ ንጉሠ ጽዮን።

ልጅዎ ልጅ ኢያሱ አልጋ ወራሽ ከሆኑ ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ የሚሠሩት ሥራ ሁሉ የልጅ ሥራ እንደሆነ ንጉሡም ያውቁታል። እኛም መክረን ተቆጥተን እናሳድጋለን ብለን ብናስብ ባንድ ስፍራ የማይቀመጡ ስለሆነብን ጊዜ አላገኘንም። አንዳንድ ጊዜም እያገኘን ብንመክራቸው አልተቀበሉንም። እኛም ምናልባት ከነገ ሣልስት የመንግሥታቸውን ጥቅም፤ የራሳቸውን ማዕረግና ክብር እያወቁ ይህን የልጅነት ሥራቸውን ይተውት ይሆናል በማለት ሰውነታቸው እንዳይሳቀቅ ታግሰን ብንጠብቃቸው የልጅነት ሥራ መሥራታቸው አልበቃ አላቸው። ... ይህንንም ሁሉ ታግሰን ሁላችንም ባንድነት ሆነን ሊቀ ጳጳሱንና እጨጌውን ጨምረን ለማናቸውም ቢሆን ለእንቁጣጣሽ (ላዲሱ አመት) ወደ አዲስ አበባ ይምጡ ብለን ደብዳቤ ጽፈን ብንልክላቸውም ሳይመጡ ቀሩ። ይህንም ሁሉ ለንጉሥ መጻፋችን አጼ ምኒልክን እኛንም ሁሉ እንዲወዱ እናውቃለንና አሳብዎ ከአሳባችን ሳይለይ በአንድነት እንድንቆም እንጂ በተለየ ንጉሥ እንዲቀየሙና ልጅ ኢያሱ እንዲጎዱ ብለን ያደረግነው አይደለም። መስከረም 24 ቀን 1909 ዓ.ም...››

ከ7 ዓመታት በፊት መስከረም 25 ቀን 2009 ዓ.ም ወደር በሌለው የጦር ሜዳ ጀግንነታቸው የሚታወሱት ብርጋዴር ጀኔራል ለገሰ ተፈራ ወልደሥላሴ አረፉ።

አምስት የሶማሊያ ተዋጊ ሄሊኮፕተሮችን ያጋዩት፣ የሶማሊያን ተዋጊ ጄቶች እርስ በእርሳቸው አላትመው ያነደዱት፣ ጀት አብራሪው እና የበረራ አስተማሪው፣ የሐረር ጦር አካዳሚ ምሩቁ፣ ሳይሰለቹ የመብረር፣ በአየር ላይ የመገለባበጥ፣ ዒላማ የማስገባትና ምንም ጭስ ሳያሳዩ የማረፍ ልዩ ተሰጥኦዎች ባለቤቱ፣ የፕሬዚዳንት ራውል ካስትሮ ልዩ እንግዳና ተሸላሚው፣ ወደር የሌለው የኅብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ከፍተኛ የጀግና ሜዳይ ተሸላሚው፣ ‹‹ሸንቃጣው፣ ሽቅርቅሩና መልከ መልካሙ›› የሚባሉት፣ የወይዘሮ አልማዝ አምሃ ባል፣ የነፃነት እና የሉሊት አባት፣ ጀግናው ብርጋዴር ጀኔራል ለገሰ ተፈራ የዚህ ሳምንት የታሪክ አካል ናቸው።

ከ50 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መስከረም 26 ቀን 1966 ዓ.ም ‹‹የዮም ኪፑር›› ወይም ‹‹የረመዳን›› ጦርነት በመባል የሚታወቀው አራተኛው የዐረብ እሥራኤል ጦርነት ተጀመረ።

ጦርነቱ በግብፅ እና በሶሪያ የሚመራው የዐረብ ሀገራት ጥምረት፣ በእሥራኤል የዮምኪፑር በዓል ቀን፣ በእሥራኤል ላይ ጥቃት ሲሰነዝር የተጀመረ ሲሆን፣ ውጤቱም የእሥራኤልን አሸናፊነትና የዐረቦችን ተሸናፊነት ያሳየ ነበር። በአንዳንድ ተንታኞችም ግብጽ ከጦርነቱ መጠነኛ ጥቅም አግኝታለች ይባላል።

በዚሁ ቀን መስከረም 26 ቀን 1974 ዓ.ም የግብጽ ፕሬዚዳንት የነበሩት አንዋር ሳዳት ተገደሉ። ሳዳት የተገደሉት በመጀመሪያዎቹ ቀናት መጠነኛ ድሎችን ያገኙበትንና ከሞታቸው ቀን ልክ 8 ዓመታት በፊት የተጀመረውን የዮም ኪፑር ጦርነት 8ኛ ዓመት መታሰቢያ እያከበሩ ሳለ ነበር።

በካሊድ እስላምቡሊ የተመሩት የሳዳት ገዳዮች፣ ሳዳት ከዮም ኪፑር ጦርነት በኋላ ከእሥራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ሜናኸም ቤጊን ጋር የተፈራረሙትን የካምፕ ዴቪድ የሰላም ስምምነትን አምርረው የተቃወሙ ፀረ እሥራኤል አክራሪዎች ናቸው።

ከ8 ዓመታት በፊት መስከረም 27 ቀን 2008 ዓ.ም አንጋፋው ጋዜጠኛ፣ ዲፕሎማትና የታሪክ ጸሐፊ አምባሳደር ዘውዴ ረታ ወልደአረጋይ አረፉ። አምባሳደር ዘውዴ ረታ ‹‹የኤርትራ ጉዳይ›› በሚለው ግዙፍ መጽሐፍ እና በሌሎች የታሪክ መጽሐፎቻቸው እንዲሁም በዲፕሎማትነታቸው ይታወቃሉ።

# በሙዚቃው ‹‹ኦሴ ባሳ›› የሚጠራው አቀንቃኝ

ቤዛ እሸቱ

እናቱና አባቱ ተስማምተው በሀገር ወግ መጠሪያ እንዲሆነው ያወጡለት ሥም ጸጋዬ ይሰኛል። ሙሉ መጠሪያው ጸጋዬ ሥሜ። ድምጻዊ የግጥምና ዜማ ደራሲነት ደግሞ የተሰጠው መክሊቶቹና መተዳደሪያው ናቸው። በቀድሞው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በቅርቡ በአዲስ አደረጃጀት የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በሚል በተደራጀው ክልል ውስጥ ሶዶ ወረዳ ኑረና ጎርጊዜ ተብሎ የሚጠራው አካባቢ የትውልድ ቦታው ነው።

የአምስት ዓመት ልጅ ሳለ መኖሪያውን ከተወለደበት አካባቢ ወደ አዲስ አበባ በመቀየር በቄስ ትምህርት ቤት የፊደል ጉዞውን ሀ ብሎ ጀመረ። ገሊላ ትምህርት ቤት፣ ቅዱስ ጳውሎስ፣ እቴጌ መነን ትምህርት ቤት እስከ ስምንተኛ ክፍል እውቀት የቀሰመባቸው ትምህርት ቤቶቹ ናቸው። በመቀጠል ባመራበት አዲስ ከተማ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እስከ 12ኛ ክፍል ተምሯል። በጄነራል ዊንጌት ለአራት አመታት የጂኤም ትምህርቱን ተከታትሎ ዲፕሎማ አግኝቷል።

ግን በዚህ ሁሉ የትምህርት ቤት ቆይታው ጸጋዬና የክበባት ተሳትፎ ጭራሽ አይተዋወቁም። የእሱ ዋና አላማ ትምህርት ተምሮ በተማረው ትምህርት ሀገሩን ማገልገል ነበር። በሰፈርም በትምህርት ቤት አካባቢም ትርፍ ሰዓት ሲያገኝ እግር ኳስ መጫወት ያስደስተዋል። ሰፈር ውስጥ በሚደረጉ ሠርግና መሰል ዝግጅቶች ልቡ እስኪጠፋ ይጨፍራል። ዘፈን ለመዝፈን አስቦም አልሞም አያውቅም። በቃ ድግስ ካለ እሱ በጭፈራ የዚያ ድግስ አድማቂ ነው። ለመተዳደሪያ ደግሞ የተማረበት የሥራ መስክ ላይ ይሰማራል፤ እቅዱም ህልሙም ፍላጎቱም ይህ ነበር።

ከአምስት ዓመቱ ጀምሮ የአዲስ አበባ ነዋሪ ቢሆንም በየክረምቱ ወደ ትውልድ አካባቢው መሄድ የዓመት ከዓመት ልማዱ ነው። በጋ በአዲስ አበባ ትምህርቱን ሲከታተል ይቆያል ክረምት ላይ በመደበኛነት ሀገር ቤት ይገባል። እዚያ እንደልቡ ይጫወታል ከጨዋታ በዘለለም የክስታንኛ ቋንቋውን አዳበረ። አዲስ አበባ ሲመለስም በተደጋጋሚ ቋንቋውን የሚችሉ ሰዎችን እየፈለገ ስለሚያወራ መለያ ሥሙ ‘ጸጋዬ ክስታኔው’ ሆነ።

በ1982 ዓ.ም ከዊንጌት መመረቁን ተከትሎ ከቤተሰብ ጫና በመውጣት የራሱን ገቢ ለማመንጨት ጓጉቷል። በሀገሪቷ የለውጥ ወቅት አየሩን ተቆጣጥሮታል፤ እሱ ግን እራሱን ሊችል ስለሆነ ሃሳቡ በሙሉ እራስ መቻል ላይ ነበር። ከተማረበት ትምህርት ቤት ሥም ዝርዝራቸው ተወስዶ በአምቦ የጦር መሣሪያ መገጣጠሚያ ፋብሪካ ሥራ እንደሚጀምሩ ተነግሯቸው ልቡ ጮቤ ረግጧል። ለቤተሰቡ የመጀመሪያ ልጅ እንደመሆኑ የቤተሰብ ደጀን ሆኖ የታናናሾቹ መከታ ሊሆን ተዘጋጅቷል። እሱን ያዩ ታናናሾቹ በሱ ፈለግ እንደሚከተሉ በማሰብ ተደስቷል።

ግን ይህ ሁሉ ጮቤ መርገጥ ሳይሰምር ቀረ። የዚህ ምክንያቱም ሹፌር የነበሩት ወላጅ አባቱ በዚህ ቀውጢ ሰዓት ምን ሲደረግ መሣሪያ ፋብሪካ ትቀጠራለህ አይሆንም አሉ። የዚህ ምክንያታቸው የመሣሪያ ፋብሪካዎች በግጭት ወቅት ጥቃት ይደርስባቸዋል ብለው በመስጋት የበኩር ልጃቸውን እንዳያጡ መፍራታቸው ነው። የኔን ደመወዝ አካፍልሀለሁ እንጂ እያየሁ ለሞት አልከህም በማለት ልጃቸውን በአዲስ አበባ ለማቆየት ወሰኑ።

ክስታኔኛ በደንብ መቻሉ ጠቅሞት የክስታኔ ልማት ማኅበር በክስታንኛ ቋንቋ በሚያዘጋጀው ጋዜጣ ላይ በጋዜጠኝነት መሥራት ጀመረ። ታዲያ ያኔ የማኅበሩ አባል የነበሩትና በዘርፉ የዳበረ ልምድ ያላቸው ተክሉ ታቦር በጋዜጠኝነት ለመሰማራት እንዲያስችለው ለአንድ ሳምንት የጋዜጠኝነት ሥልጠና ሰጥተውታል። ጸጋዬ ክስታንኛ በደንብ ይችላል፤ በክስታንኛ ግጥም ይጽፋል፤ ዘፈኖችን ያንጎራጉራል። ግን ‹‹አንድም ቀን ዘፋኝ እሆናለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር›› ይላል።

በ1988 ዓ.ም የዋለው የፋሲካ ዋዜማ ግን ከሌሎች የበዓል ሰሞኖች ሁሉ ይለያል። ከጓደኞቹ ጋር ሰብሰብ ብለው ለመዝናናት በማሰብ አብነት አካባቢ የሚገኝ የምሽት ክበብ ይገባሉ። ዕለቱ የበዓል ዋዜማ ነውና ቤቱ በሰው ተሞልቷል። ጸጋዬና ጓደኞቹ እንደሌሎቹ ተዝናኞች ከምግቡም ከመጠጡም እየወሰዱ ዘና ብለዋል። ከምንም በላይ ደግሞ በቤቱ የሙዚቃ ባንድ መኖሩ ተመችቷቸዋል።

በሙዚቃውም በመጠጡም እየተዝናኑ ነው። በዚህ መሃል የጉራጊኛ ዘፈን ሊዘፍን አንድ ልጅ ወደመድረክ ይወጣል። ልጁ ቋንቋውን በደንብ ባለማወቁ በትክክል እየዘፈነው አይደለም። በዚህ የተናደደው ጸጋዬ ልጁ ከመድረክ ሲወርድ ጠብቆ የዘፈነው ቋንቋ ትክክል አለመሆኑን ይነግረዋል። ከፈለገ ትክክለኛውን ግጥም ሊጽፍለት እንደሚችል ቃል ይገባለታል። በመሃል ለምን እኔ አስተካክዬ አልዘፍነውም በሚል ወኔ መድረክ ላይ ይወጣል።

ከታዳሚነት ወደ ዘፋኝነት ተሸጋግሮ እራሱን መድረክ ላይ ተበላሸ ያለውን ዘፈን ሲያስተካክል ያገኘዋል። አንድም ቀን ሳይለማመድ ለልምምድ ለባለሙያ ሳይዘፍን በመሣሪያ ተጫዋቾች ታጅቦ ለታዳሚዎች ሙዚቃን አቀረበ። ምንም እንኳን ‹ፒች ኪይ› የሚባሉ የሙዚቃ ጽንሰ ሀሳቦች ለሱ ሩቅ ቢሆኑም የአርጋው በዳሶን ዘፈን በሙዚቃ መሣሪያ ታጅቦ ዘፈነ።

ቤቱን የሞላው ታዳሚ ጸጋዬን በሽልማት አጥለቀለቀው። ከሽልማቱ በዘለለም ሁሉም ታዳሚ ብላልኝ ጠጣልኝ ባዩ ሆነ። ዘፈኑንም በታዳሚ ምርጫ በድጋሚ ዘፈነ። ያላሰበውን ሽልማት ተቀብሎ ኪሱን ሞልቶ ወደ ቤቱ ሊጓዝ ሲነሳ፤ የቡና ቤቱ ባለቤትም የቤታቸው ታዳሚ ሲደሰት ተመልክተዋልና እባክህ ነገ ና እንዳትቀር ሁሉን ወጪህን እኔ እችልሀለሁ ሲሉ አግባቡት።

በማግስቱ «የኔ ጌታ መአረይ ባክህ እንዳትቀር» ሲሉ የተማጸኑትን የቤቱ ባለቤትን ልመናና ሽልማቱን አስታውሶ በዕለተ ፋሲካ ማምሻውን ሄደ። በማግስቱም የታዳሚው አቀባበል ለየት ያለ ቢሆንበት በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ «ይሄ ነገር እንጀራዬ ይሆን እንዴ?» ሲል አሰበ። ሆኖም የዘፈን ጥናት ልምድ የለውምና ይደገም ቀርቶ ይሰለስ ቢባልም የሚያውቀውም ሆነ የሚዘፍነው ብቸኛ ዘፈን የአርጋው በዳሶ አለምብሬን ብቻ ነበር።

በወቅቱ የጸጋዬ ድምጻዊነት ከሁለት ቀናት አልዘለለም ነበር። ያም ቢሆን አብነት አካባቢ በርካታ የጉራጌ ማኅበረሰብ ስለሚኖር ጉራጊኛ የሚዘፍን ልጅ ያለበት ቤት እያሉ ሁለት ቀን የዘፈነበት ቤት ቢያመሩም ጸጋዬ ግን ሊገኝ አልቻለም። ሲያገኙትም የት ጠፋህ የሚሉት አድናቂዎች ያፈራበት የሁለት ቀን ቆይታ አድርጓል። በየመንገዱ የሚጠይቁትን ኸረ እኔ አልሠራም ለበዓል ነው የዘፈንኩት እያለ ይመልሳል። በወቅቱ በክስታንኛ ቋንቋ የሚሠራበትን የህትመት ሚድያ ማጥበቅ ምርጫው አድርጓል። በልማት ማኅበሩም የቢሮ ሠራተኛ ሆኖ ተቀጥሮ እየሠራ ነው።

በልማት ማኅበሩ አማካኝነት የክስታኔ ባንድ ሲቋቋም ከመሥራች አባሎች መሃል አንዱ ሆነ። ባንዱ ከጸጋዬ ስሜ ባሻገር ጎሳዬ ተስፋዬ፣ አብነት አጎናፍርና ሌሎችም በርካታ ሙዚቀኞችን አቅፎ ሥራ ጀመረ። ጸጋዬ የጉራጊኛ ዘፋኝ በመሆን ባንዱን ተቀላቀለ፤ ለሱም የኪነጥበብ መንገድ ተጀመረ። እንሾሽላ ሠርግ መልስ ሲባል አብዛኛውን ቀን የሥራ ቀናቸው እንደነበርና በሳምንት ረቡዕን ብቻ ያርፉ እንደነበር ያስታውሳል።

ጸጋዬ ችላ ካላት መክሊቴ ብሎ ብዙም ዋጋ ካልከፈለላት ሙዚቃ ጋር በባንዱ አማካኝነት በደንብ ተግባብቷል። መድረክና ዝግጅት ላይ ከመሥራት በዘለለም ክስታኔ ሲሉ የሰየሙትን የመጀመሪያ አልበማቸውን በባንዱ አማካኝነት ሦስት ድምጻውያን ተጣምረው ለአድማጭ እንካችሁ አሉ። አልበሙ ሙሉ የሙዚቃ መሣሪያ ገብቶበት የተቀረጸ ሲሆን የአልበሙ



አርቲስት ፀጋዬ ስሜ፤

ፎቶ- ገባቦ ገብሬ

አብዛኛው ክፍል የተቀናበረው የባንዱ ኪቦርዲስት በነበረው ድምጻዊ አብነት አጎናፍር ነበር።

ጸጋዬ ክስታኔ ባንድ እየሠራ ነጠል ብሎ ለብቻው ሁለተኛ አልበሙን አወጣ። የሕዝቡ ተቀባይነት እየጎላ ሲመጣና በየቦታው ፈላጊው ሲበዛ ከባንድ ተቀጣሪነት ወደ ባንድ ባለቤትነት ተሸጋገረ። የራሱን ባንድ ‹እስኝታ› ባንድ ሲል መሠረተ። ያም ቢሆን የመጀመሪያውንና ባለውለታውን የማይረሳው ድምጻዊ ክስታኔ ባንድ ዛሬ ባይኖርም ከሕዝብ ጋር ያስታዋወቀኝ ባለውለታዬ በማለት ያስታውሰዋል።

በ1996 ዓ.ም ጳጉሜ አራት የወጣው የጸጋዬ ሦስተኛ አልበም የሙዚቃውንም ሆነ የሕይወቱ ማርሽ ቀያሪ አልበም ነው። የአልበሙ መጠሪያ እንሾሽላ ሲሰኝ የድምጻዊው መጠሪያ እስኪሆን የታወቀበት ኦሴ ባሳ የተሰኘው ሙዚቃ የተካተተበት ነው። ድምጻዊው ‹‹ኦሴ ባሳ ከጉራጌ ማኅበረሰብ አልፎ በመላው ኢትዮጵያውያን እንድታወቅ ያደረገኝ ዘፈን ነው›› ይላል።

«መጠሪያዬ በኦሴባሳ መተካቱን አድናቆት ስለሆነ እቀበለዋለሁ እንጂ ቃሉ ለሰው ልጅ አይሆንም።» በማለት ኦሴባሳ ትርጉሙ ነውር ነው ማለት እንደሆነ ያስረዳል። በወቅቱ ብዙ ነውር የሆኑ ነገሮችን በማስተዋሉ ነውር ነው ለማለት በድፍረት የጻፈውና የተጫወተው ዘፈኑ ነው። በዘፈኑ የሚያየውና የሚሰማው ነገር በሙሉ አስቀያሚ ነገር መሆኑን ይጠቅሳል።

ድምጻዊው በጉራጌ ማኅበረሰብ ዘንድ ሴት ልጅ ሳታገባ ካረገዘች፣ ስርቆት ካጋጠመ፣ ባጠቃላይ መሆን ያልነበረበት ነገር ሲሆን ከታየ ትልልቅ ሰዎች ‹‹ይሄ ኦሴባሳ ነው›› እንደሚሉና የማውገዣ ቃል መሆኑን ያነሳል። በዘፈኑ ጆሮዬ መጥፎ ነገር አትስማ ሲል መክሮበታል። ኦሴባሳ መውጣቱን ተከትሎ ጸጋዬ በርካታ የሥራ አማራጭ የተሻለ ገቢ እንዲሁም የሕዝብ ፍቅርና እውቅና ያገኘበት ሥራው ነው። ሥራውን የሕይወቴ ለውጥ ይለዋል። ሥራው 20 ዓመት ቢጠጋውም አሁንም መድረክ ላይ በወጣ ቁጥር ሁሉ ኦሴባሳን ሳይዘፍን መውረድ የማይታሰብ መሆኑን ይናገራል። ታዳሚው ቀድሞ ኦሴባሳ ይላል። ጸጋዬን ያየ ታዳሚ ኦሴባሳን እንደሚሰማ እርግጠኛ ይሆናል።

ዬሻለ የተሰኘው አራተኛ አልበሙን በ2000 ዓ.ም ለአድማጭ አድርሷል። በ2005 ዓ.ም የወጣው ‹ጥምቡስ አሳብ› አምስተኛ አልበሙ ሲሆን፤ የመጨረሻው አልበሙ ‹ሱታና› ይሰኛል። ድምጻዊው በሀገር ውስጥ በበርካታ ከተሞች ተዘዋውሮ ሥራዎቹን አቅርቧል። በባህር ማዶም በጀርመን ፍራንክፈርትና ሙኒክ ላይ ሥራዎቹን አቀንቅኗል። ባህሬን፣ ኳታር፣ ዱባይ ኤርትራ ታዳሚዎቹን አዝናንቷል።

እንደ ሙዚቃ ሕይወቱ ሁሉ የሰመረ ትዳር አለው። የትዳር አጋሩን የተዋወቃት ሙዚቃ ጥሪው መሆኗን ሳያውቅ በዊንጌት ትምህርቱን ሲከታተል ነው። ያኔ እሷም በትምህርት ቤቱ የአካውንቲንግ ተማሪ ነበረች። የያኔ የፍቅር ጓደኛው የአሁን የትዳር አጋሩ አስቴር ታደሰ። በተማሪነት ዘመናቸው የተጀመረው ፍቅር ወደ ጋብቻ ሳያመራ ድፍን አስር ዓመት በፍቅር ጓደኝነት ቆይተዋል። ሁሉን አደላድለው የጀመሩት ትዳር በፍሬ ተባርኮ የአንድ ሴት ልጅ ወላጆች ሆነዋል።

በቡታጅራ መስመር በምትገኘው ቡዒ ከተማ የገነባው ኦሴባሳ ሆቴል ተመርቆ ሥራ ከጀመረ አንድ ዓመት ተሻግሯል። በቀጣይነት ለኑሮ መደጎሚያ ከሱ የሙዚቃ ሥራና ከባለቤቱ መደበኛ ሥራ ተጨማሪ ደጓሚ እንደሚሆናቸው ተስፋ አድርጓል። ድሮ ክትፎ ዋነኛ የምግብ ምርጫው ነበር። ዕድሜ ጨመር እያለ መሄዱን ተከትሎ የምግብ ምርጫው በጎመን ክትፎና በአይብ ተተክቷል። ሁሉንም ሥራዎቼን እወዳለሁ የሚለው ድምጻዊው አጥብቆ ለጠየቀው ግን ‹‹ኸዲስ ባለአገር ነውን›› የተለየ እንደሚወደው ምስጢር ያወጣል።ኸዲስ ባለአገርነው (እኔ ባላገር) ኦሴባሳ የሚገኝበት ሦስተኛ አልበሙ ላይ የተካተተ ሥራው ሲሆን አስተዳደጉን የሚገልጽበትና አሁንም ባላገር ነኝ የሚልበት ተወዳጅ ዘፈኑ ነው።

# ዓለም አቀፍ

## በኒው ዮርክ ከተማ በተከሰተ ከባድ ጎርፍ ሳቢያ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ተደነገገ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በአሜሪካዋ የኒው ዮርክ ከተማ የተከሰተው ከባድ ውሽንፍር ድንገተኛ ጎርፍ በማስከተሉ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ተደነገገ።

የከተማው በርካታ የምድር ውስጥ የባቡር መስመሮች በጎርፍ የተሞሉ ሲሆን፣ የፍጥነት መንገዶችም በውሃ ተጥለቅልቀዋል። በዚህም ምክንያት በከተማዋ ካሉ አየር ማረፊያዎች መካከል ቢያንስ አንዱ ትናንት አርብ ተዘግቷል።

በከተማው አንዳንድ አካባቢዎች ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ የጣለ ሲሆን፣ ትናንት ምሽት ዝቅተኛ መጠን ያለው ዝናብ በሌሎችም ስፍራዎች ሊኖር እንደሚችል ተንበያ ተሰጥቷል።

የኒው ዮርክ ገዢ ካቲ ሆቹል በኤክስ ወይም በትዊተር ገጻቸው ባሰፈሩት መልዕክት «በመላው ኒው ዮርክ፣ ሎንግ አይላንድ እና በሃድሰን ቫሊ አካባቢ በተከሰተው ከፍተኛ ዝናብ ምክንያት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅን ተደንግጓል» ብለዋል።

አገረ ገዢዋ ሰዎች ደኅንነቱ በተጠበቀ ስፍራ እንዲቆዩ እና በጎርፍ በተሞሉ መንገዶች እንዳይጓዙም አሳስበዋል።



በጎርፉ ምክንያት እስካሁን ሞት ወይም ከፍተኛ ጉዳት አልተመዘገበም።

ከኒው ዮርክ ከተማ በቅርብ ርቀት ላይ በሚገኘው የኒው ጀርሲ ሆቦከን ከተማም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ተጥሏል። የኒው ዮርክ ከተማ ከንቲባ ኤሪክ አደምስ በበኩላቸው ሰዎች በከፍተኛ ጥንቃቄ እና ንቃት መቆየት ይገባቸዋል ሲሉ አሳስበዋል።

ከንቲባው የከተማዋ የባቡር መስመሮች ከልክ በላይ እንደተጨናነቁ እና በከተማው ውስጥ መዘዋወር አስቸጋሪ እንደሆነ ገልጸዋል።

ከንቲባ አዳምስ አርብ ምሽት በጎርፉ ምክንያት መውጫ ያጡ 15 ሰዎችን ከተሽከርካሪዎች እና ከምድር ላይ ከሚገኝ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ክፍል ውስጥ መታደግ መቻሉን ለመገናኛ ብዙኃን ተናግረዋል።

የከተማው የትራንስፖርት ኤጀንሲ እንዳወጣው መረጃ ከሆነ ከፍተኛ ጎርፍ የኒው ዮርክ ከተማ ዋነኛ የባቡር መስመሮችን በከፍተኛ ሁኔታ አስተጓጉሏል። የተወሰኑ የምድር ውስጥ የባቡር መስመሮች ሙሉ በሙሉ የተዘጉ ሲሆን፣ በርካታ የባቡር ጣቢያዎች ዝግ ተደርገዋል።

በአንዳንድ አካባቢዎች የድንገተኛ አደጋ ጊዜ ሠራተኞች በሕንፃዎች ውስጥ በጎርፍ መውጫ ያጡ ሰዎችን ለመታደግ ተንሳፋፊ ጀልባዎችን መጠቀማቸውም ተዘግቧል።

በርካታ አካባቢዎች ላይ ሰዎች በጎርፍ እስከጉልበታቸው ጠልቀው መውጫ በማጣት ግራ ሲጋቡ የሚያሳዩ ፎቶ እና ቪዲዮዎች በማኅበራዊ ትስስር ገጾች ታይተዋል።

የኒው ዮርክ ከተማ ፖሊስ በርካታ መንገዶች ዝግ እንደተደረጉ እና የሀገሪቱ ብሔራዊ ዘብ መሰማራቱን ገልጿል።

በኒውዮርክ እ.አ.አ. ከ1882 ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ እጅግ እርጠበት አዘል የሆነ አየር ንበረት በመስከረም ወር ላይ ተመዝግቧል።



## ተመራማሪዎች የስድስት ሺህ ዓመታት ዕድሜ ያለው ጥንታዊ ጫማ አገኙ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ስድስት ሺህ ዓመታት ገደማ ዕድሜ አለው ተብሎ የተገመተ ከሳር የተሠራ ጥንታዊ ጫማ በስፔን በአንድ ዋሻ ውስጥ ማግኘታቸውን ተመራማሪዎች አስታወቁ።

በአውሮፓ ውስጥ ከተገኙ ቀደምት ጫማዎች መካከል በዕድሜ ቀዳሚ ነው የተባለው ይህ ጫማ ስፔን ውስጥ በሚገኝ የሌሊት ወፎች ዋሻ ውስጥ ነው የተገኘው።

በ19ኛው ክፍለ ዘመን በማዕድን አውጪዎች ተዘርፏል ከተባለው ዋሻ ውስጥ በርካታ የተለያዩ ዓይነት ጥንታዊ ቁሶች ከጫማው በተጨማሪ በተመራማሪዎቹ ተገኝተዋል።

በዋሻው ውስጥ ያለው ዝቅተኛ እርጥበት እና ነፋስ ባልተለመደ ሁኔታ ጥንታዊ ቁሶቹን ሳይበለሳሹ እንዲቆዩ እንዳደረጋቸው ባለሙያዎቹ ገልጸዋል።

ተመራማሪው ማሪያ አታል የተገኙት ቁሶች «እስካሁን በደቡባዊ አውሮፓ ባሉበት ሁኔታ መገኘታቸው ከታወቁ የዕፀዋት ውጤቶች መካከል በዕድሜ ቀዳሚዎቹ ናቸው» ብለዋል።

ጨምረውም እነዚህ ግኝቶች ላይ «ጥቅም ላይ የዋሉት የተለያዩ ዓይነት ዘዴዎች እና የጥሬ ዕቃዎች አዘገጃጀት ረገድ ቅድመ ታሪክ ማኅበረሰቦች ያላቸውን ክህሎት ለማየት ይቻላል» ሲሉ ተናግረዋል።

በዋሻው ውስጥ የተገኙትን 76 ቁሶች መሆናቸውን ጠቁመው፤ የቁሶቹን ዕድሜ ለማወቅ ጥቅም ላይ የዋለው አዲስ ቴክኖሎጂ እንዳረጋገጠው፣ ቀደም ሲል ከተገመተው በላይ ሁለት ሺህ ዓመት ዕድሜ እንዳላቸው ተገልጿል።

አንዳንዶቹ ቁሶችም ዘጠኝ ሺህ ዓመት እንደቆዩ ተመራማሪዎቹ ገልጸዋል። በተገኘው ነጠላ ጫማ ላይ በተደረገው ምርምር ጫማውን ለመሥራት የተለያዩ የሳር ዓይነቶች ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በተጨማሪ ቆዳ እና ኖራ ተገኝቶበታል ተብሏል።

ስድስት ሺህ ዓመት ዕድሜ አለው የተባለው ጫማ በደቡባዊ ምዕራብ ስፔን አንዳሉሺያ ግዛት በሚገኝ ዋሻ ነው የተገኘው።

በተመራማሪዎቹ ጥናት መሠረት ሰው መጀመሪያ ላይ ወደ ዋሻው የገባው በ1831 የአፈር ማዳበሪያ ለማዘጋጀት የሌሊት ወፎችን ዐይነ ምድር ለመሰብሰብ ነበር።

ከዚያም በኋላ ማዕድን አውጪዎች ወደ ዋሻው በመግባት የተለያዩ ጥንታዊ ቅርሶችን ለማግኘት መቻላቸው ይነገራል።

# ስፖርት


## የሴቶች ማራቶን ክብረወሰን ከየት እስከ የት?

ብርሃን ፈይሳ

ባለፉት ሁለት የዓለም ቻምፒዮናዎች በሴቶች ማራቶን አሸናፊ የሆነችው ኢትዮጵያ ባለፈው ሳምንት የርቀቱ የሴቶች የዓለም ክብረወሰ ለመጀመሪያ ጊዜ እጅዋ ገብቷል። በኢትዮጵያ ሴቶች የአትሌቲክስ ታሪክ በዚህ ርቀት ክብረወሰን ሲሰበር ይህ የመጀመሪያው ሲሆን፤ ይህንን ያሳካችው አትሌት ትዕግስት አሰፋ ከመላው ዓለም ዛሬም ድረስ አድናቆት እየተቸራት ይገኛል። በተለይም አዲሱ የትዕግስት ክብረወሰን በሴቶች ማራቶን አትሌቶች በታሪክ ከ2 ሰዓት ከ10 ደቂቃ በታች የማጠናቀቅ ተስፋ ማሳየቱ ዋነኛው ምክንያት ነው። ከዚህ ጋር ታያይዞም የዛሬው የአዲስ ዘመን ስፖርት ማህደር ትኩረቱን በሴቶች የማራቶን ክብረወሰን ሂደት ላይ ያደርጋል።

ከስፖርታዊ ውድድሮች ፈታኙ፣ ከሩጫ ስፖርቶች ደግሞ ረጅም በሆነው ማራቶን አዳዲስ ክብረወሰኖችን ለማስመዝገብ የሚያስፈልገውን ልፋትና የብቃት ጥግ መገንዘብ ቀላል ነው። ታዲያ ከፍተኛ ጽናትና ቁርጠኝነትን በሚጠይቀው በዚህ ውድድር በዓመታት ውስጥ የሚመዘገበው የሰዓት ልዩነት አስደናቂ የሚባልም ነው። ለአብነት ያህል በ19ኛው ክፍለዘመን ወንዶች ማራቶንን ለ3 ሰዓት ጥቂት ደቂቃዎች በሚቀሩት ሰዓት ይሸፈን ነበር። ከመቶ ዓመት በኋላ ግን ይህ ሰዓት ተሻሽሎ ከ2 ሰዓት በታች ለመግባት የቀረው 1 ደቂቃ ብቻ ነው። ከዚህም በመነሳት በርቀቱ አዲስ ሰዓት ማስመዝገብ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል።

ይህ ሁኔታ በሴቶች በኩል ሲታይ ግን ሌላ መልክ አለው። ማራቶንን እንዲሮጡ ከመፍቀድ አንስቶ ክብረወሰን እስከማሻሻል ባለው ረጅም ሂደት ሲመዘን ከወንዶቹ አንጻር በእርግጥም ዘርፈብዙ ለውጦች ታይተዋል። ምክንያቱም ወንዶች በኦሊምፒክ ማራቶንን




**የትዕግስት አሰፋ 2:11:53 ሰዓት ስሌሳ አዲስ ክብረወሰን ተስፋ ሰጪ ሆኗል፣**

መሮጥ ከጀመሩበት ወደ 100 ዓመታት ከሚጠጋ ጊዜ በኋላ ነው ሴቶች ርቀቱን የተቀላቀሉት። አንዳንድ መዛግብት የሴቶች ማራቶንን ለመጀመሪያ ጊዜ ከወንዶች እኩል የመሮጥ ታሪክ የተመዘገበው በቦስተን ማራቶን መሆኑን ያትታሉ። በወቅቱ ለወንዶች ብቻ በተፈቀደው ውድድር ወንድ በመምሰል እንዲሁም ከጸጥታ ኃይሎች ጋር ግብግብ በመግጠም ጭምርም ነበር የመጀመሪያዋ ሴት ርቀቱን የሸፈነችው። ይህ ከሆነ ከአምስት ዓመታት በኋላም ሴቶች ከወንዶች እኩል መወዳደር እንደሚችሉ ታምኖበት በኦሊምፒክ እንዲወዳደሩ መደረጉንም መዛግብት ያስነብባሉ።

እውቁ የአትሌቲክስ መጽሔት ራነርስ ወርልድ በበኩሉ በዓለም አትሌቲክስ ዕውቅናን ያገኘው የመጀመሪያው ውድድርና የመጀመሪያዋ ሴት አትሌት የተመዘገቡት እአአ በ1926 መሆኑን ያስነብባል። እንግሊዛዊቷ ቫዮሌት ፔርሲ የተሰኘችው አትሌት በወቅቱ ርቀቱን ለመሸፈን የፈጀባትም ጊዜ 3:40:22 ነበረ። ይህ አሁን አትሌቶች ከሚገቡበት ጊዜ አንጻር ሲታይ እጅግ ከፍተኛ ለውጥ ያለው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ይሁንና በስፖርቱ ታሪክ የትኛዋ ሴት በየትኛው ውድድር ማራቶንን ለመጀመሪያ ጊዜ ሮጠች የሚለውን በትክክል በማስረጃ አስደግፎ ማቅረብ አይቻልም። ምክንያቱ ደግሞ ከክርስቶስ ልደት በፊት ይደረግ በነበረው የጥንታዊው ኦሊምፒክም ጥቂት ሴቶች የወንዶቹ ውድድር ከተካሄደ በኋላ ይሞካከሩ እንደነበር የተለያዩ ጽሑፎች ስለሚያስነብቡ ነው።

በዘመናዊው ዓለምም ቢሆን በመላው ዓለም ጎልቶ ከሚታወቀው የቦስተን ማራቶኑ ታሪክ አስቀድሞ እንደእነ ፔርሲ ያሉ ሴቶች በተለያዩ የማራቶን ውድድሮች ላይ መሳተፋቸው ይታወሳል። ይሁንና በዓለም አቀፍ የስፖርት ማኅበራት እውቅና ባለማግኘታቸው ምክንያት ታሪካቸው ከመዳፈኑ ባለፈ ርቀቱን የሸፈኑበት ሰዓትም በትክክል ባለመታወቁ ልዩነቱን ለመረዳት አዳጋች ይሆናል። ኦሊምፒክን እንደ መነሻ ካደረግን ግን እአአ በ1984 በተካሄደው የሎስአንጀለስ ማራቶን ለመጀመሪያ ጊዜ በተካሄደው የሴቶች ውድደር በአሜሪካዊቷ አትሌት ጆን ቤኖይት የተመዘገበው ሰዓት 2:24:52 የሆነ ነበር። ነገር ግን ኦሊምፒኩ ከመካሄዱ አንድ ዓመት አስቀድሞ በተጀመረው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና አሸናፊ የነበረችው ኖርዌያዊት አትሌት ግሬቴ ዊትዝ 2:28:09 የሆነ ሰዓት ነበር። ይህ ከሆነ ለ4 አስርት ዓመታት የተጠጋ ጊዜ ቢቆጠርም ግን የሴቶች የማራቶን ሩጫ ከውስን ደቂቃዎች በላይ ለውጥ ሊመጣበት እንዳልቻለ መገንዘብ ይቻላል።

ከ2ሰዓት ከ20 ደቂቃ በታች ለመጀመሪያ ጊዜ ሴቶች የሮጡት እአአ 1979 ሲሆን፤ በ2ሰዓት ከ19 ደቂቃ ርቀቱን ለመሸፈን ደግሞ 22 ዓመታት ተቆጥረዋል። እአአ ከ1970ዎቹ ወዲህ ባሉት ዓመታት አዳዲስ ክብረወሰን የተመዘገበባቸውን ጊዜያት ስንመለከትም እየሰፋ መምጣቱን ያሳያል። ይኸውም ማራቶንን ከ2 ሰዓት በታች ለመግባት በወንዶች በኩል ከሚደረገው ጥረት እና ከፍተኛ ፉክክር አንጻር በሴቶች በኩል ከ2 ሰዓት ከ10 ደቂቃ በታች ለመግባት የሚደረገው ጥረት እምብዛም ሊባል የሚችል ነው። ይሁንና ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ትዕግስት አሰፋ ቀድሞ ከነበረው ሰዓት ወደ 3 ደቂቃ ፈጥና 2:11:53 በሆነ ሰዓት መግባቷ ተስፋ ሰጪ ሆኗል። አትሌቷ ካላት ጽናትና ብቃት አንጻርም ይህ ሰዓት በራሷ ይሻሻላል በሚልም በስፖርት ቤተሰቡ ዘንድ ይጠበቃል።




# ‹‹ውቢቷ ኢትዮጵያ ለልጆች›› የልጆች መጽሐፍ

እየሩስ ተስፋዬ

ሠላም ልጆች እንዴት ናችሁ? አዲሱን የትምህርት ዓመት እንዴት እያሳለፋችሁት ነው? በጥናት እና በንባብ እያሳለፋችሁት እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለኝም። ልጆችዬ ብዙ ጊዜ ስለ ንባብ ጥቅም አውርተናችኋል አይደል? ዛሬ ደግሞ እናንተ ልጆች ብታነቡት ስለ ኢትዮጵያ ብዙ ነገር እንደምታውቁበት መረጃ ስለያዘው መጽሐፍ የተወሰኑ መረጃዎችን እንሰጣችኋለን እሺ።

ልጆችዬ «ውቢቷ ኢትዮጵያ ለልጆች» በሚል ርዕስ የተዘጋጀ የሕፃናት መጽሐፍ መስከረም 12 ቀን/2016ዓ.ም ተመርቆ ለንባብ በቅቷል። መጽሐፉ በአራት ምዕራፍ የተከፋፈል ሲሆን፤ አንደኛው ምዕራፍ ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ስለ ምትታወቅባቸው ነገሮች፣ ምዕራፍ ሁለት አዲስ አበባ እና በውስጧ የሚገኙ ሐውልቶችን እንዲሁም ሙዚየሞችን አካቷል። ምዕራፍ ሦስት ኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚገኙ የቱሪስት መዳረሻዎች የሚዘረዝር ሲሆን፤ የመጨረሻው ምዕራፍ ደግሞ ባህላዊ የሆኑ የማይዳሰሱ መስህቦችን በዝርዝር አካቷል። ደራሲው አይነ ስውር ልጆች እንዲያነቡት በማሰብም በብሬል አዘጋጅቷል።

የመጽሐፉ ጸሐፊ መምህርና የሕግ ባለሙያ ሞገስ ጌትነት እንዳሉት፤ ልጆች አካባቢያቸውንና የሀገራቸውን ባህል እንዲያውቁ እና ብዙ ጊዜ የሕፃናት መጻሕፍት ሲጻፉ ተረቶች ላይ ያዘነበሉ በመሆናቸው ታሪካቸውንና ባህላቸውን የሚያስገነዝቡ መጻሕፍትም አስፈላጊ በመሆናቸው መጽሐፉ ተጽፏል።

ወላጆች ልጆቻቸው በሚያነቡበት ወቅት፤ በቅርበት ቢሆኑ ስለሚያነቡት ነገር በመወያየት ግንዛቤያቸው እንዲጨምር ያግዛቸዋል። በተጨማሪም አቅማቸው የሚፈቀድ ከሆነ ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሠራሽ ቅርሶችን በአቅራቢያቸው የሚገኙትንም የመስህብ ስፍራዎች እንዲጎበኙ እንደሚያግዛቸው ደራሲው አስታውቀዋል።

ወላጆችም ልጆቻቸውን ከቀለም ትምህርት ባለፈ




ሁለንተናዊ ዕውቀት እንዲያዳብሩ መጻሕፍትን ለልጆቻቸው ማስነበብ እንዳለባቸው በማስገንዘብ፤ ዕውቀታቸውን እንዲያዳብሩም እንደዚህ ዓይነት መጻሕፍትን በመግዛት ለልጆቻቸው ማስነበብ እንዳለባቸው መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

በመጽሐፉ ምርቃት ወቅት የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር ዋና ሥራ አስኪያጅ ደራሲ የዝና ወርቁ ታደሰ ደግሞ፤ ታሪኩን የሚያውቅና በሥነ-ምግባር የታነጸ ትውልድ ለማፍራት፤ ልጆች በቀላሉ ሊረዷቸው የሚችሉ የሕፃናት መጽሐፍትን ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው። እናም ልጆች፤ የሕፃናት መጽሐፍትን ለማዘጋጀት ከቋንቋ አጠቃቀም ጀምሮ ልዩ ጥንቃቄና ዕውቀትን በሚጠይቅበት ሁኔታ እና በሥዕላዊ መረጃ አስደግፎ ደራሲው መጽሐፉን ማቅረቡን ጠቁመዋል።

‹‹ሀገር የራሷ መልክ እና ቅርጽ ያላት ሆና የምትቀጥለው በልጆች ነው። ትውልድ ያልፋል፤ ትውልድ ይተካል። በልጆች አእምሮ ተቀርጾ የሚተላለፉ መለያ ማንነታችን እና እሴቶቻችን ናቸው።›› ያሉት ሥራ አስኪያጇ፤ ማንነቱን ያወቀ እና የለየ ትውልድ ለማስቀጠል በጣም ብዙ ስልቶችን መጠቀም እንደሚገባም ገልጸዋል። ‹‹በቤተሰብ ውስጥ የሚከወን ሥነ ቃል፣ ተረት እና ለልጆች ታሪክን መንገር የሚያስፈልግ ቢሆንም፤ አብዛኛው ወላጅ (አሳዳጊ) ለልጁ ‹‹ተረት ተረት›› የመነገር ችሎታ የለውም። ከችሎታ ባለፈም ጊዜም የለውም። ስለዚህም ይህንን ኃላፊነት መወጣት የሚቻለው የሕፃናት መጽሐፍትን በማዘጋጀት ነው። በራሳቸው የሚተማመኑ ሀገራቸው እና ወገናቸውን የሚወዱ በሥነ ምግባር የታነጹ ዜጋ ለማፍራት የሕፃናት እና የታዳጊዎችን መጽሐፍት ማሳተም መተኪያ የሌለው ዐቢይ ሥራ ነው›› ሲሉ ለልጆች የሚታተሙት መጽሐፍት ትኩረት አናሳ እንደሆነ እና ትውልድን በሥነ - ጽሑፍ መቅረጽ እንደሚገባ አሳስበዋል።

ልጆችዬ በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የልጆች መጽሐፍ የተጻፈው ጥቅምት 16 ቀን/ 1916 ዓ.ም ሲሆን፤ መቶ ዓመት ሊያስቆጥር ጥቂት ቀናት ብቻ ናቸው የቀሩት። ‹‹የፍቅር መላዕክት ለኢትዮጵያ ልጆች›› በሚል ርዕስ በአማርኛ ቋንቋ በበቀለ ሀብተ ሚካአል ሲታተም፤ አንድነት ኃይል እንደሆነ፣ ስለጊዜ ጥቅም፣ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ በማስተዋል እና በጥበብ መፍታት እንደሚገባ የሚያመላክት እንደሆነ ሥራ አስኪያጇ አስታውሰዋል።

አሁን ላይ ግን መጽሐፍ የሚያነቡ እና ለልጆች መጽሐፍ የሚገዙ ወላጆች ቁጥር አናሳ ነው። ስለዚህም ጊዜውን፣ ገንዘቡን እና እውቀቱን በመጠቀም የትውልድ ኃላፊነቱን ለተወጣው ደራሲ ምስጋናቸውን በማቅረብ፤ ሥነ ጽሑፍ የሰዎችን አእምሮ በማዝናናት እና በማስተማር መልካም አስተሳሰብ እንዲሰርጽ ለማገዝ ድርሻ እንዳለው የዝና ወርቁ አስረድተዋል።

ደራሲ እና ጋዜጠኛ ጥበቡ በለጠ በበኩላቸው፤ ደራሲው ‹‹ውቢቷ ኢትዮጵያ ለልጆች›› የተሰኘው መጽሐፍ፤ ልጆችን በሚመጥን መልኩ መዘጋጀቱን በመግለጽ፤ እንደዚህ ለልጆች ስለ ሀገራቸው የሚጻፉ መጽሐፍት ልጆች ስለሀገራቸው ያላቸውን ግንዛቤ ከፍ ያደርጋሉ ሲሉ ገልጸዋል። አሁን ላይም ልጆች ላይ መሥራት ግድ የሚልበት ወቅት ላይ እንደምንገኝም ጠቁመዋል።

ልጆችዬ በመጽሐፉ ዙሪያ አስተያየታቸውን ከሰጡት መካከል ኮሜድያን አስረስ በቀል (ቼሪ) ይጠቀሳሉ። እርሳቸው እንዳሉት ደራሲው ልጆች ኢትዮጵያን በሚጣፍጥ፣ አጭር እና ግልጽ በሆነ መንገድ እንዲያውቁት አዘጋጅቶታል። ይህን ዓይነት ሥራ በማቅረቡ የሚያስመሰግነው እንደሆነ በመግለጽ፤ የልጆች ንባብ እንዲስፋፋ ትምህርት ቤቶች የልጆች መጽሐፍትን በመግዛት የንባብ ባህል እንዲዳብር መሥራት እንዳለባቸውም አስገንዝበዋል።